# ምዕራፍ አራት

## የአለት አምባ፣ አንግዳ የሆነ ተፈጥሮ፣ ስመልፈንገስ በፎቃዳ፣ የአቢሲኒያ ቤተክርስቲያንና የቀብር ስነ ሥርአት

ካፒቴኑንና ተጓዦችን ስደርስባቸው፣ ካፒቴኑ፣ ሀሰን በሚባል ወደፊት መንገድ ስመቀጠል ፈቃደኛ ባልሆነ አገልጋይ በጣም ተበሳጭቶ ነው ያገኘሁት።

ጠቆር ያለው የሀገሩ መሬት አንደአውነቱ ከሆነ አስፈሪ ገፅታ ነው ያለው። ከደረቁ ጥቂት ችፍንች በስተቀር ተክል የሚባል ነገር ፈፅሞ የተራቆተ ነው። ድንጋያማ በሆነ መሬት ብዙ ማይሎች ርቀት የሚሆን ተጓዝን። በግራ በኩል፣ ለብዙ ማይሎች በመንገዳችን ጎን አብሮን የሚሄድ በአለቶች መሀከል የተቦረቦረ በየጊዜው ድንገት የሚታጠፍ ሸለቆ ነበር፤ በቀኛችን በኩል ደግሞ አርባ ማይል ርቀት የሚሆን ጨለም ብለው በውል የማይለዩ የአድዋ ተራራዎች ይታያሉ።

የአራት ሰአታት ጉዞ ከአንድ ጋራ ስር አደረሰን። ጋራው፣ ያቋረጥነውን ደረቅ መሬት ከመሰለ ቦታ ላይ ወደ ላይ ከፍ ብሎ እንደ ጅብራልታር የቆመ ነው። በሁሉም ጎኑ ለመከላከል አመቺ በሆነ ቀጥ ባሉ ገደሎች ነው የተከበበው፤ ዝቅተኛው ቦታ እንኳን ቢሆን ከመሬቱ ሶስት መቶ ጫማ ከፍታ አለው።

አንድ ሺ ጫማ ርቀት ከሚገኘው ሸጠጥ ብሎ ወጣ ያለ ኮረብታ በስተቀር ሌላ ጋራውን መቆጣጠር የሚቻልበት ቦታ የለም። ካለው ስፋት አንፃር ወደ አስር ሺ የሚሆኑ ወታደሮች ሊያስፍር ይችላል። ለምን እንዲህ አይነቱ በተፈጥሮ የማይደፈር ቦታ በአቢሲኒያው ንጉሥ በቴዎድሮስ እንዳልተያዘ በጊዜው በሃሳቤ ጥያቄ የፈጠረ ነገር ነበር። እንጣሎ የሚባል ቦታ እስከደርስ ድረስ የሀገሪቱ ፖለቲካ በውል አልገባኝም ነበር።

በዚህ ቦታ በደቡባዊ ምሥራቅ ጠርዙ በኩል የአንድ ማይል ተኩል ርዝመት ያለው የኮረብታዎች ስንሰለት ይታያል፤ ላዩም በአጫጭር ዛፎችና የጥድ ዛፎች ተሸፍኗል። በጎንና በጎኑ በኩል ደግሞ ጠበብ ያሉ ሸለቆዎች፣ ስሬ የተባለው ቦታ እንኳን አንድ ማይል የማይሞላ ቀጥ ባሉ የ600 ጫማ ጥልቀት ያላቸው ገደሎች የተመሠረተ ነው። ሸለቆዎቹ ስፋ እያሉ ይሄዱና ዘርጋ ያለ ሜዳማ ቦታዎችና ዛፎች የሞሉበት በውስጡ ወራጅ ውሀዎች የሚፈሱበት ቦታ



ይከፈታሉ። በዚህ ሥፍራ ለአደን የሚሆኑ የተለያዩ እንስሳት ሞልተውበታል። በዚህ በሸለቆው፣ የፎቃዳ መንደርና ቤተክርስቲያን ይገኛሉ። በአጠገቡ፣ ከፍ ባለው ቦታ ላይ የፈረሰኞች ካምፓኒ ድንኳኖች ተተክለው ይታያሉ። የወታደሮቹ ካምፕ መሆኑ ነው። በርከት ያሉ የጉድጓድ ውሀዎችን በመቆፍር ውሀ እንደልብ ለማግኘት ተችሏል፤ ውሃውም ሰፋ ያለ ማጠራቀሚያ ላይ ተሞልቶ እንስሳቶችን በሙሉ ማጠጣት ተችሏል።

ፎቃዳ ካምፕ የደረስነው ፀሀይ ከመጥለቋ ከሁለት ሰአታት በፊት ነበር። ሻይ በበቂ መጠን ከጠጣን በኋላ፣ ከዚህም ጋር ምቾት ወዳጁ ካፒቴኑ ጓደኛዬ ያዘጋጀውን የተቀመመ ምግብና የሥጋ ጥብስ ከበላን በኋላ ያሳለፍነውን ችግር በፍጥነት ረሳነው።

ፎቃዳ በጣም የሚስብና የሚያስደስት ቦታ ነበር። ካፒቴኑና እኔም ከረዥም ውይይት በኋላ፣ ለሳምንት ወይም ከዛ በላይ ምንም አይነት ወታደራዊ እንቅስቃሴ ስለማይኖር እኛም ለሁለት ወይም ለሶስት ቀናት በዚሁ ቦታ ለመቆየት ወሰን።

የተከበረው ጓደኛዬ፣ የመጀመሪያውን ቀን ያሳለፈው ከጉና ጉና ጉዞ በኋላ በአሳዛኝ ሁኔታ ተጠርፎ የመጣውን የራሱን ጓዝ በማውረድ ነው። በርከት ያሉ ዕርድና ሌሎች ቅመሞችን የያዙ ጠርሙሶች በመንገዱ ላይ በደረሰባቸው መንገጫገጭ ተሰባብረዋል። በዚህ ምክንያት፣ የሰውየው ነጎድጓድ የሆነ የርግማን ጩኸት ከአድለቢሶች አሽከሮቹ ጆሮ አልፎ ተሻግሮ ወደ መቅደላ አቅጣጫ በሳይንሳዊ መንገድ ቢነጣጠርና ቢለቀቅ መቅደላን ብትንትኑን ባወጣው ነበር።

አጋጣሚ ሆኖ፣ የምግብ ባልንጀራ አስገራሚ ጓደኛዬ አደን በጣም የሚያደንቅና የሚወድ ስለነበር በፎቃዳ ቆይታችን አብዛኛውን ጊዜ በአደን አሳለፈው። ማታ ሲመለስ፣ በአደኑ ያጋጠመው ገድል፣ እንደሱ አገላለፅ፣ ጠቀም ያለ የፅሁፍ አምድ ይሞላ ነበር። በመጀመሪያው ቀን ሁለት አነሮች፣ ቀለማም የሆነ ኩምቢው ተለቅ ያለ የወፍ ዝርያዎች፣ ሰባት አርግቦች፣ አንድ ጅብ፣ አንደ ቀበሮ እና የዱር ጥንቸል ገድሏል። ወደ ቤት ይዟቸው ከመጣቸው መሀል፤ እኔ የምመሰክረለት አንድ ኮሳሳ ጥንቸል፣ ሶስት ብጥስጥስ ያሉ አርግቦች እና አንድ ትልቅ አሞራ አለበት። አሞራው ሲለካ፣ በጀርባው ከላባው ጫፍ እስከ ኩምቢው ጫፍ ድረስ፣ አምስት ጫማ ርዝመት አለው። አብሮት የሄደውን አሊን ስጠይቅ ግን፣ እንደ እሱ አመላለስ ካፒቴኑ ወደ ቤት ይዟቸው ከመጣቸው ውጭ ሌላ ሲገድል አላየሁም ብሎ ነገረኝ። ምናልባትም በአሊ ደካማ የአይን ችግር ምክንያት ሊሆን ይችላል።

በፎቃዳ ቆይታችን በሁለተኛው ቀን፣ ከፍ ያለ ድምፅና ጩኸት ከመንደሩ አቅጣጫ ይሰማን ጀመር:: ካምፑም የተሰየመው በዚሁ በመንደሩ ስም ነው:: የፎቃዳ መንደር ከኛ በትንሹ ወደግራ በኩል ባለ ኮረብታ ላይ ነው የተመሰረተው:: ወዳለንበት ካምፕ የሚያመራውን መታጠፊያ መንገድ መቆጣጠር የሚቻልበት ቦታ ላይ ነው ያለው:: ከጋራው ግርጌ ቤተክርሰቲያን አለ:: ይህ ደግሞ ከሰናፌ ወደ አንጣሎ በሚወስደው መንገድ የመጀመሪያው የአቢሲኒያ ቤተክርስቲያን ነው:: ቤተክርሰቲያኑ ዙሪያውን በዛፎች ታጅቦ፣ ጠበብ ያለ ከፍተት ጠርዝ ላይ ነው ያለው:: ይህ ከፍተት ከቤተክርሰቲያኑ ትንሽ ያርዶች ርቀት ይጀምርና እየሰፋ በመሄድ ትልቅ ሸለቆ ይሆናል:: በሸለቆውና በቤተክርሰቲያኑ መሀከል የኗሪዎቹ አነስ ያለ የመቃብር ቦታ አለ::

የኛ ድንኳን የተተከለው በካምፑና በመንደሩ መሀከል አጋማሽ ቦታ ነው፤ ሰለዚህ የካምፑና የመንደሩ ጥሩ ዕይታ አለን:: ጩኸቱ እየጎላ መጣ፤ ከዚያም በረድፍ የሚመጡ ሰዎች ወንዶችም ሆነ ሴቶች ጭንቅላቶቹ ቁልቁሰቱን ሲወርዱ ይታየን ጀመር:: ሰዎቹ በዝግታ ነበር የሚጓዙት:: አሁንም አሁንም፣ ቆም እያሉ የጀሮ ታምቡር የሚበሳ ጩኸትና አሳዛኝ ድምፅ ያሰማሉ:: ጉዳዩ ምን እንደሆን ከጠየቅሁና የቀብር ስነ ሥርአት መሆኑን ካረጋገጥኩ በኋላ፣ ሥርአቱን በደንብ ለማየት ከፍታ ቦታ ላይ ወጣሁ::

ትንሹም ትልቁም ተደምሮ ወደ መቶ ሃምሳ የሚሆኑ ሰዎች በጥቂት ካህናት እየተመሩ ይጓዛሉ:: እነዚህ የአቢሲኒያ የቤተክህነት ሰዎች የለበሱት፣ በተለመደው በሥርአት የሚለበስ ረጅም ከጥጥ የተሰራ ቀሚስና ከአንገታቸው ዙሪያ ጀምሮ ሙሉ ሰውነታቸው ላይ የሚወርድ ሰፋ ያለ ሻወል በማድረግ ነው:: ቀባሪዎቹ ደግሞ የሚወራጩ ይመስላሉ፤ ላያቸው ላይ የለበሱትን ልብስ ይቀዳሉ፤ ፀጉራቸውን ይነጫሉ፤ እጃቸውን ደረታቸው ላይ አጣምረው መግለፅ በማይቻል ሁኔታ የሀዘን ምልክት ይታይባቸዋል:: በተለያዩ ምስሎችና ፅሁፎች የተሞሉ በብራና በደንብ የተጠረዙ መፅሀፍቶች በእጃቸው ይዘዋል:: ፅሁፉም በአራቢክ[71] ቋንቋ ነው:: መፅሐፎች አሁንም አሁንም እየተገለጡ ለሚወዷቸው ቅዱሳን ፀሎት ያደርሳሉ፤ ረዘም ያለ ፀሎቱም በጠንካራ የሳምባ እስትንፋስ፣ አፍንጫ ላይ ያዝ በሚያደርግ በሚያሰዛን ድምፅና ማነብነብ ነው የሚካሄደው:: ይህ ሥርአት ለሁለት ደቂቃ የሚሆን ከተደረገ በኋላ፣ ካህናቱ እንደማንጎበስ ብለው አንደገና ጉዟቸውን ይቀጥላሉ:: በየተወሰኑ ርቀቶች አንደመንበርከክ ይሉና ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ በሚያሳዝን ሁኔታ ዜማ ያሰማሉ::

---

[71] ፀሐፊው ግዕዝ የሚባል ቋንቋ መኖሩን ያወቀ አይመስልም



የመቃብሩ ቦታ ሲቃረቡ፤ አስከሬኑን የተሸከሙት፣ ፀጉራቸው ላይ ሽበት የሚታይባቸው ሰዎች ወደ ጉድጓዱ ጠጋ አድርገው አወረዱት:: እስከሬኑ በሕይወት እያለ ሲለብሰው በነበረው ሸማ ተጠቅሏል:: ከዚያ ቀጥሎ ካህናቱ ፀሎት ያሰሙ ጀመር ሲተረጎም እንደሚከተለው ነው::

"ወርቅነህ፣ የእያሱ ልጅ አሱም የተከኤ ልጅ እርፏል፤ እነሆም እመስግኑ፤ ከአብርሃም፣ ከይስሐቅና ከያቆብ ጋራ ለመሆን ወደ እረፍቱ ሄዷል:: በሕይወት ላሉት አንፀልይ፤ ነፍሳቸው ለተኮነነው አንፀልይ:: ነፍሱ ከፍርድና ከቅጣት ትድን ዘንድ አንፀልይ:: ነፍሱስ ከፍዳ እንዴት ትተርፋለች? እጥብቆ በመፀለይ:: በአብርሃም ጥላ ሥር እንዲሆን፣ በሙሴ ጎን በሰላም አንዲራመድ ከነብያቶችም ጋር፤ ፀልዩ፣ አሜን እሜን::"

መቃብሩም ተዘጋ፣ ላዩም ላይ የአፈር ቁልል ተከምሯል፤ ዙሪያውን ደግሞ ሞልሞል ያሉ ድንጋዩች ከተደረገ በኋላ፣ በግርጌና በራስጌው ጠፍጠፍ ያሉ ድንጋዮች አንዲቆሙ ተደረገ:: ቀባሪ ተበተነ:: እብዛኛው ሰው ደግሞ የሚያነቃቃ ዜማ የሚያዜመውን ሰው ተከትሎ ነው የሄደው:: ከዚህ ትኩስ መቃብር ተነስቼ ወደቤተክርስቲያኑ አመራሁ:: ፀሎትና ዜማ ሲያደርሱ ከነበሩት ካህናት አንደኛው ወዲያውኑ የኔ አጃቢና አስጎብኝ እንዲሆን ተመደበልኝ::

ለጉብኝቱ፣ መጀመሪያ፣ በአዲሱ የማርትሬዛ ዶላር ከፍያ መደረግ ነበረበት:: ዋጋው ሲነፃፀር በስምንት ሳንቲሞች ከአሜሪካው ዶላር በላይ ይሆናል::

በሁለት ትልልቅ የዋርካ ዛፎች የተሸፈነ ቅስት አልፈን ወደ ቅጥር ግቢው ገባን፤ ለክርስትና አምነት ፀሎትና ሥርአት የተከለለ ቦታ መሆኑ ነው::

እንደውነቱ ከሆነ አንዳችም የቤተክርስቲያን ምልከት፣ ማለትም ከትልቁ ካቴድራል ጀምሮ በየትኛውም የአለም ክፍል፣ ከአፍሪቃ በስተቀር፣ የሚገኝ የመስብሰቢያ ቦታ ጋር እንኳን የማይገናኝ ነው:: ቁሸሽ ያለና ያልፀዳ፣ በፎቃዳ፣ በቅዱስ ሚካኤል ስም የተሠራ ነው:: በበሩ በኩል አንድ ርምጃ ወደ ውስጥ ለተራመደ ሰው፣ ቃል የማይገልፀው የሚያሳዝንና የተረሳ ቦታ መሆኑን ማንም መረዳት ይችላል::

ፎቃዳ በመጣን በሰሰተኛው ቀን፣ በጥዋት ተነስተን፣ ጓዛችን ሸከፈን፣ ካለንበት የአስር ማይሎች ይርቃል ወደተባለው፣ የሚቀጥለው ጣቢያ፣ ወደ አዲግራት መንገድ ጀመርን::

ይህን መንገድ ለጠረጉት ሰዎች ድካም በቂ ምከንያት ነበረ:: ለወታደራዊ ጉዞ እንደዚህ ያለ አሰቻጋሪ ምድር ማግኘት ይከብዳል:: የመንገዱ እያንዳንዱ ማይል የተዘረጋው በጠንካራ ንጣፍ አለት ላይ ሲሆን፣ አለቱ ደግሞ በተለያየ

አቅጣጫ እንደ ጥርስ ፍሩግሩግ ብለው ወደላይ ሾል ሾል ብለው ወጣ በማለት በሚታዩ የአለቱ ክፍሎች የተሞላ ነው፡፡ የድንጋይ መፍለጫ መሳሪያዎች እዚህ ቦታ በጣም ያስፈልጉ ነበር፤ ቀለል ያሉ ቦታዎችን በዚህ የአለት ቦታ ላይ ወደ መንገድ ለመቀየር ብዙ ስልትና ጥበብ ያስፈልግ ነበር፡፡ መንገዱም፣ በሾላ፣ በቁልቋልና በሌሎች ትልልቅ ዛፎች በኩል አልፎ ይሄዳል፡፡ ተጨርሶ ሲታይ፣ የሚያስገርም የወታደራዊ ምህንድስና ሥራ ነው የሆነው፡፡ ወደ ጎን፣ ስፋቱ 15 ጫማዎች ሲሆን፣ በተቻለ መጠንና የአካባቢው ሁኔታ በሚፈቅድው ላዩ ለስለስ ያለ እንዲሆን ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ በሰልፍ የሚጓዙት ወታደሮች በቀላሉ ሊራመዱበትና የማጓጓዣ ጋሪዎችም ቢሆኑ ከባህሩ ደንበር ተነስተው አዲግራት ድረስ ሊሄዱበት ይችላሉ፡፡

ከዚህ መንደር አንድ ማይል ርቀት ካለፍን በኋላ፣ ጎድጎድ ያለ ቦታ ደረስንና ቁልቁለቱን በዝግታ ወረድን፡፡ በዚህ ሥፍራ፣ በጉዟችን ለመጀሪያ ጊዜ አረንጓዴ በቆሎ አየን፡፡ ሰፋ ያለ ቦታ ሆኖ፣ በሥርአት በተቆፈረ መስኖ ውሀ ይጠጣ ነበር፡፡

በዚህ ሰፋ ባለና ፈገግ በሚያስደርግ እይታ፣ ጣራቸው ዝቅ ያሉ ቤቶች እጅብ ብለው ይታያሉ፤ እኔም ወደነሱ አቅጣጫ መራመድ ጀመርኩ፡፡ ወፎች በደስታ ይዘምራሉ፤ ከምዕራብ አቅጣጫ በሚነፍሰው ነፋስ፣ የበቆሎ ተክሎች ይወዛወዛሉ፤ የፀሀይ ሙቀቱም ቢሆን ላዩ ላይ ልክ ባህር ላይ እንደሚወዛወዝ ውሃ ጥላ፣ በእርሻው ላይ ሲርገበገብ ይታያል፡፡

በቦታው እንደደረስኩ፣ ጠየም ያሉ፣ ፀጉራቸው ጭንቅላታቸው ጀርባ ላይ የተጎነጎነ ሴቶች ልጆች፣ ነጣ ያልነውን ፀጉረ ልውጥ ሰዎች ለማየት ከበቡን፡፡ ልጆቹም፣ ልክ ከየትም የአሜሪካ ትምህርት ቤት የሚመለሱ ልጃገረዶች እንደሚያደርጉት በጩኸትና ፍንድቅድቅ በማለት ነበር የተሰበሰቡት፡፡ ራቁታቸውን የሆኑ ትንንሽ ልጆች ደግሞ መጡ፤ እነሱም የሰውነት እንቅስቃሴ ችሎታቸውን ለነዚህ የተለዩ እንግዶች ለማሳየት፣ እየተፈናጠሩና እየተዟዟሩ ነበር፡፡ እኔም "ሀሊብ" ወይም ወተት እንዳለ ጠየቅሁ; የተለመደውን አዲስ ገንዘብ "ግርሽ" ለመክፈል ፈቃደኛ መሆኔንም ገለፅኩ፡፡

አንዲት ወጣት ሴት ልጅ፣ እንደ ሄብ ረጋ ባለ ሁኔታ ወተቱን ሰጠችኝ፡፡ እኔም እንደተጠማ ሰው በማጣጣም በደንብ አድርጌ ጠጣሁ፡፡

እኩለ ቀን ሲሆን፣ የሰር ናፒየር ዋና ጽ/ቤት ያለበት አዲግራትን ማየት የምንችልበት ቦታ ደረስን፡፡

የተጓዝነው መንገድ አጭር ስለነበር፣ ተጨማሪ ጉዞ ለማድረግ ወሰንና፣ ከማቆማችን በፊት በኮሎኔል ፋይሪ ከሚመራው ቀዳሚ ወገን ለመድረስ ሙከራ አደረግን፡፡ ካፒቴኑ በመንገዳችን ላይ ሁለት ደርዘን የሚሆኑ እርግቦች

በመግደል ለሰር ሮበርት ናፒየር ስጦታ ሊያቀርብ ነው። እሱ ወደካምፑ ሲሄድ፡ እኔ ደግሞ ወደ ቀኝ ታጠፍኩና የአዲግራት መንደርን ለማየት ሄድኩ።

አዲግራት የተቀመጠችው፣ በሰፊ ሜዳ መሀከል ላይ ባለ አነስ ያለ ከፍታ ቦታ ላይ ነው። የቦታው ዋናው ገፅታ፣ ከጭቃ በተመረቱ ጡቦች የተሠራ ግምብ ቤት ነው። በአንድ ጎኑ፣ ግምቡ አራት ማዕዘን የሆነ ሰቀላ ያለው ሲሆን፡ ከአናቱ ላይ አራት ወጣ ወጣ ያሉ የተገነቡ ነገሮች አሉት። በሠለጠነ አይን ላየው፣ ለመከላከያ ወይም ለጥንካሬ የተገነባ ከመምሰል ይልቅ ለምስል ውበት ነው የሚመስለው።

እኛ ቤቱን አልፈን በሄድንበት ጊዜ፣ በቴዎድሮስ ቁጥጥር ስር የሆነ ጌታ ሚስት ትኖርበታለች። ባሏ ስሌለ፣ ሴትዮዋ በሀዘን የምትፅናና አይነት አልነበረችም፤ ስለዚህ ባሏ ተመልሶ ሀዘንተኛውን ልቧን እስከሚያስደስተው ድረስ፡ ፀሀይ ሆነ ዝናብ ራሷን እንዳይነካት መሀላ ገብታ ከቤቱም አትወጣም።

*(ለአንባቢዎች ተጨማሪ ቃል ለመስጠት፣ የምገልፀው ነገር ቢኖር የዚህ ቤት ጌታ መቅደላ ሲያዝ የተለቀቀ ሲሆን፣ አዲግራት መጥቶ የቤቱን ግንብ ሲገነባ ፀሀፊዊም በተመሳሳይ ጊዜ አዲግራት ደርሶ ነበር።)*

ከዚህ መከላከያ አጠገብ ቤተክርስቲያን ነበር፤ ያለምንም ጥርጥር ከጨለሉቶት በስተቀር በአቢሲኒያ ካየኋቸው ቤተክርስቲያናት በሙሉ የሚያምር ነው። ዙሪያውን በቁልቋል ተክሎች የተከበበ ነው፤ የቁልቋሎች ጥላ ራሱ የሚያነቅ ሲሆን፣ ላካባቢው ሰላማዊ የሚያረጋጋ ስሜት ፈጥሮበታል። ቄሶቹ የተከበሩና ሽምገል ያሉ ሆነው፣ በራሳቸው ላይ ቀጥ ያለ ከፍታ ያለው ከመጠን በላይ ገዘፍ ያለ ጥምጣም አድርገዋል። እነሱም መጥተው በሰላምታ ተቀበሉኝ።

ቤተክርስቲያናቸውን ለማየት ባለኝ ፍላጎት የተለመደው መደለያ ተሰጥቶ፣ ለስጦታየም ምክንያቱን ለማስረዳት ባደረግሁት የሰውነት እንቅስቃሴ ተገልፆ ነው። እነዚህ በጥቅሻና በሰውነት እንቅስቃሴ መግባባቶችን አንድ ሰው በቀላሉ ነው የሚማራቸው። በተጨማሪም ለትውውቅ የሚረዱ ታላቅ ነገሮች ናቸው፤ በዚህ መንገድ የሀገሪቱ የምኞት ነገሮች ለምሳሌ ወተት፣ እንቁላል፤ አይብ፤ ዳቦ እና አጃ የመሳሰሉትን፣ የገንዘብ ንብረት በፈቀደው መጠን እንዳገኝ ይረዳል።

ቄሶቹ የስጦታዬን ምክንያት ተገንዝበዋል፤ በመግቢያው በኩል በተክሎቹ መሀል አልፈው ወደ ከፍት ገላጣው ቦታ እቅጣጫ ሲሄዱ እኔም ተከተልኳቸው። ንፁህ ገላጣውን ቦታ አልፈው፣ ወደ ውስጥ በሚያስገባው በአራት ማዕዘን በር አልፍን ሄድን፤ መራመድ ለሰውነት እንቅስቃሴ ሲሉ

የሚያደርጉት እንጂ የተፈጥሯቸው ያልሆነ ይመስል ቄሶቹ እርስ በራሳቸው እየተሳለፉ ነው የሚሄዱት::

በቤቱ መግቢያ ወይም በረንዳ በኩል ካለፍን በኋላ፣ ከውስጥ በኩል በቤተክርስቲያኑ ዙሪያ የሚዞር ከፍት አዳራሽ ወስጥ ገባን:: የዚህ ከብ የሆ ቤተክርስቲያን ግድግዳ የተሠራው በድንጋይ ሆኖ፣ ላዩ አንድ ኢንች ውፍረት ባለው ጭቃ ተስስኖ በተቻለ መጠን ለስላሳ እንዲሆን ለማድረግ ተሞክሯል::

በዚህ ጸሎት ቤት፣ የአቢሲኒያ ምስሎች ባልተለመዱ መሳሪያዎች ተስለዋል:: መጀመሪያ የቅድስ ጊዮርጊስ ምስል ድራጎኑን በፈረሱ እግር ርግጦ ይታያል፤ የሚያደንቁ ታላላቅ ሰዎችና ሴቶች በቡድን ሆነው፣ በፊታቸው ላይ ጥልቅ የሆነ የርካታ ስሜት እያሳዩ፣ ሰው በላው ጠላት ሲገደል አያዩ ነው:: ሁለተኛው ሰዕል ፀሎተ ሀሙስ ነው፣ 13 ደቀመዝሙሮች አራት ሲበሉ በሚደነቅ ሁኔታ ነው የተሳለው:: ሶስተኛው ስዕል፣ ቅዱስ ጴጥሮስ ሲሰቀል የሚያሳይ ነው:: በዚህ በከፋ መስዋዕትነት፣ የቅዱስ ጴጥሮስ ስቃይ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ፣ የአቢሲኒያው ሰአሊ፣ ስቃይ የደረሰበትን ሰው ገፅታ ለመሳል ብዙ የደከመ መሆኑን ያሳያል:: በግድግዳው ላይ ሌሎች ስዕሎችም ነበሩ፤ እነሱም ስእምነታቸው ሲሉ መስዋዕትነት ሲከፍሉ ነው የሚያሳየው:: ባልተባረከው አይኔ የቅዱሶችን ቅዱስ ቦታ ከማየቴ በፊት፣ ሌላ ዶላር ተጠየቅሁኝ፤ ግብሩን ከከፈልኩ በኋላ ቄሱ ወደ ውስጥ፣ በከቡ መሀል፣ ወደ መቅደሱ ወሰደኝ:: በቄሱ እየተመራሁም ዙሪያውን ተራመድኩኝ::

ስአይን የሚታይ ምንም እስደናቂ ነገር እልነበረም:: ከፊት ሰፊቱ ከነሀስ የተሠራ ትልቅ መስቀል ያሰበት አንደነገሩ የሆነ ጠረጴዛ እስ፤ ይህም ቄሶች በሰንበት ቀን የሚቀድሱበት ነው፤ ሰንበት የሚውሰውም ቅዳሜ ቅዳሜ ነው:: ትልቅ በቆዳ የተጠረዘ መፅሀፍ እስ፤ መፅሀፍ ቅዱስ ይሆናል፤ ታጥፎ አትሮኖሱ ላይ ተቀምጧል:: ወለሉ ንፁህም እልነበረም፤ እንዳንድ ቦታ ላይ ገለባ ተበትኖ ይታያል፤ አኔን የመሰለኝ፣ አንድ የማይረባ ወሮበላ እንደ መኝታ የተጠቀመበት ነበር::

ከቤተክርስቲያኑ ወደ ውጭ ወጣሁ፤ ቤተክርስቲያኑና ግምብ ቤቱ ከተሠራበት ከዚህ ከፍታ ላይ ሆኖ የአዲግራት ጠቅላላ ሜዳው ይታያል:: በመሀከሉም፣ እንደ በረዶ ቁልል፣ የእንግሊዝ ሠራዊት ንፁህ ነጭ ድንኳኖች ይታያሉ:: ወታደሮቹም እስከዚህ ድረስ በጄኔራሉ እየተመሩ የመጡት የሀገራቸውን ሰዎች ለማስለቀቅ ነው::

እሁንም አሁንም፣ ለየት ያለ ሳቅ ይሰማል፤ የእንግሊዝ ሰዎች አይነት ነው፤ በጣም ጎርነን ያለ በመሆኑ፣ ከሩቅ ሲሰማ ስውነቱ ግዙፍ ከሆነ ሰው የሚመጣ የማያቋርጥ ሳቅ ይመስላል:: ቀይ ዩኒፎርም የለበሱ ወታደሮችና





*በማይ ዋሂዝና በአዳ አባጋ መካከል የሚገኝ ግምብ ቤት*

ዘቦች በእጃቸው የሚያብረቀርቅ ብረት ይዘው፣ በአንዳንዶቹ ዋና ጽ/ቤት ክፍሎች አካባቢ ወዲያና ወዲህ ሲመላለሱ ይታያሉ፤ አለዚያም ባተኮሩ አይኖቻቸው የስንቅና ጥትቅ ከፊሉን ቦታ ይመለከታሉ፤ ይህ ቦታ እንግዲህ የዘመቻው ዋናው ጅማት ቦታ ነው:: ያማረ ዩኒፎርም የለበሱ መኮንኖች፣ በጎኖቻቸው የያዟቸውን ሾተሎች እና የፈረስ መኮልኮያቸውን እያንኳኩ፣ በፈረስ ላይ ሆነው እየተጣደፉ ሲመጡና ሲሄዱ ይታያል፤ እነሱም መልከቶችን ለተለያዩ የሬጅምንት ክፍሎች ለማድረስ ነበር:: በመቶዎች የሚቆጠሩ ፈረሶችና በቅሎዎች በተርታ ታስረው በረሃብ እያናፋና አየጮሁ የሚቀርብላቸውን መጠነኛ መኖ ይጠብቃሉ:: እሁን እኩለ ቀን ስለሆነ፣ ውሀ

የሚጠጡበትና የሚመገቡት ሰአት ነበር:: በቁጥር ብዛት ያላቸው ያገሩ ተወላጆች፣ ላይናቸው እንግዳ የሆነውን ነገር በጉጉት ለማየት ሰብሰብ ሰብሰብ ብለው ቆመዋል፤ ስላዩት እንግዳ የሆነ ነገር እየተነጋገሩ ነበር ለማለት እደፍራለሁ::

ከዚህ በአቢሲኒያ ሜዳ እንግዳ የሆነና የሚያነቃቃ ዕይታ ጥቂት ማይሎች እለፍ ብሎ፣ ደፋር ተራሮች ወደ ጠርዝና ገደል የመሰለ ቦታ ይታጠፋሉ፤ ከዚያም ሆነው በወይን ጠጅ ቀለም የተጋረደ የባህር ዳር ደመና መስለው፣ በእኩለ ቀኑ ፀሀይ፣ ፀጥታ በሰፈነበት ሁኔታ ይታያሉ:: ይህንን በመመልከት፣ መግለፅ የማይቻል የትዝታ መንፈስ በሰውነት ይሰርጣል:: ከዚህ ባሻገር እንደገና፣ ተራ በተራ ወደላይ ደብዘዝ ያሉ ተራራዎች ይታያሉ፤ ምስጢራዊና እሰደናቂ በሆነ ከፍታቸው፣ በደናኪል ጨካኝ ጎሳዎችና በአቢሲኒያኖች መካከል በቂ የመከላከያ እጥር ሆነው ያገለግላሉ::

ይህንን ዕይታ እየተመለከትኩ እያለሁ፣ ለራሴና፣ ያለምንም ሀሳብና የሚያስብላቸውም በሌለበት ሁኔታ የሚጓዙትን ሠራተኞቼን እስታወስኩ:: ምንም እንኳን ራሴን ለሰር ሮበርት ናፒየር ማስተዋውቅ ብፈለግም፣ የሚሻል ሀሳብ ነው ያልኩት፣ ቀዳሚው ብርጌደ በነጋታው ስለሚጓዝ፣ እኔ ቀደም ብልና ከኛ ቀድመው መንገዱን የተያያዙትን የቃኝውን ጦር ከፍል ብጠጋ ነው:: ስለዚህ በፈረሴ ግልቢያ ጀመርኩ፤ እቧራው ሲቦን፣ እንደ እብድ የሚሯሯጡትን ልጆች ሰላስደሰታቸው፣ ፈረሱ እየተጠጋቸው ሲሄድ ከፊት ለፊቱ ይሮጣሉ:: ይህ ደግሞ፣ የኛ የሠለጠኑ ልጆች ባቡር ሲመጣ እንደ እብድ ቆመው በመጠበቅ፣ ከዚያም ሲጠጋቸው፣ ለመጨፍለቅ ጥቂት ሲቀራቸው፣ እምልጠው በመሮጥ እንደሚያሳዩት ድፍረትና አይበገሬነት ጋር ተመሳሳይ ነው::

የእዲግራትን ቤተክርስቲያንና ምኑም የማያምረውን ግምብ ቤት በመጎብኘት ያሳለፍኩት የቀን ህልም ጊዜዬን ስለወሰደብኝ፣ ሠራተኞቼ ከኋላ እስከደርስባቸው ድረስ ቀድመውኝ ብዙ ማይሎች እንዲጓዙ ረድቷቸዋል::
ከአዲግራት፣ መንገዱ በጥድና ሌሎችም ዛፎች፣ በቁልቋል ተከሎች ታጅቦ፣ ለአይን ደስ የሚያሰኝ መሀል ነው የሚወስደው:: ቦታው፣ እንደሰማነው፣ አድፍጦ ለሚጠብቅ ቀማኛ የተመቸ ነው:: ነዋሪዎቹ እንደጠቆሙን ከሆነም፣ በየቦታው የሚዘዋወሩት አሮሞዎች ምስጢራዊ በሆነ ቦታ የማይጠረጥር ሰው ድንገት እንደሚያጠቁ ነው::

ያን ቀን ባደረግነው ጉዞ እንደዛ አይነት ቀማኞችም አላጋጠመንም፤ ተጉዘንም፣ ከትልቅ ግዙፍ ከሆነ እለት ስር ባለ፣ ቅጠል የበዛበት መሹዋለኪያ ቦታ ደረስን፤ ይህም ቀጥለን ለምናደርገው ጉዞ መተላለፊያ ነበር:: በዚህ ቦታ





የእንግሊዞች ካምፕ በአዲግራት
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

መሀሉ ላይ ትንሽዋን ድንኳን ተከልንና፣ የወደቀ የዛፍ ግንድ ላይ የካምፕ እሳታችን አቀጣጠልን:: ምግብ አዘጋጆች፣ መቀቀያቸውን፣ መጥበሻቸውንና ሰሀኖቻቸውን አዘጋጁ:: አሊ የውሃ መያዣ ከረጢቱን ይዞ ንፁህ ውሃ ወደሚወርደበት ትንሽ ወራጅ ውሃ ሄደ:: የጋማ ከብቶችን የሚቆጣጠረው ሰው፣ በረዥሙ በአለትና በድንጋይ ላይ በተደረገው ጉዞ የደከመ ቢሆንም፣ ብስጭቱን የተወጣው አግባብ ያልሆኑ ቃላትን፣ እንደልቡ፣ በራሱና በፈረሶቹ ላይ ካወረደ በኋላ ነው፤ ሆኖም በመጨረሻው፣ ፈረሶችን ውሃ ለማጠጣት ይዞ ሄደ:: እኔ ደግሞ የዚህ ካምፕ ጌታ እንደመሆኔ፣ ራሴን ሞቅ በሚያደርጉ ብርድልብሶችና ከከብት ቆዳ በተሰራ መጎናፀፊያ ተጠቅልዬ፣ በትዕግሥት የካፒቴኑን መምጣት እጠብቃለሁ:: ካፒቴኑ፣ ከኔ ምንም ተቃውሞ ሳይኖር፣ ራሱን የሁሉም አላፊ አድርጎ ነው የሾመው::

በሚገርም ሁኔታ ኮስተር ብለን በራሳችን ሀሳብ ተውጠን በነበረበት ወቅት፣ መሀል ላይ፣ የካፒቴኑ ቆርጠጥ ብሎ አቀማመጥ ድንገት የነበረኝን ዕይታ አቋረጠ፣ ባልተለመደ ቀልድ፣ ብሩህ እንዲሆን አደረገው::

"በሉ በሉ፣" አለ በድንገት፣ "ለራት ምን አላችሁ? ለዘላላማዊ ሰዎች የሚሆን ያማረ እራት እናዘጋጅ፤ እኔ ምግቡን አቀቅላለሁ፣ እና አንተም አጣቢ ትሆናለህ:: ምንድን ነው የምንበላው፣ እህ?" እናም፣ ጣቶቹን ወደላይ አደርጎ፣ በእሱ እጅ ከሚገኝ ሳጥን ውስጥ ያሉ መዘጋጀት የሚችሉ ጣፋጭ ምግቦችን መቁጠር ጀመረ::

"በመጀመሪያ ይህን የመሰለ ሾርባ፣ ለዋናው ምግብ ደግሞ፣ የሚሆነንን ልመልከት፤ የጎሽ ሻኛ፣ የተቀቀለ ወርች፣ ዛሬ ከኮሚሳሪያቱ የተሠጠን እሱም ለኔ ተብሎ ነው፣ ዛሬ ካደንኳቸው የተረፈ የተቀቀለ የዳከየ ስጋ:: እህ፣ አዎ፤ ደግሞ ሌላ አሞራ አለ:: በጆሾ፣ የአሞራው ሥጋ አለ፣ ከኮሚሳሪያቱ የተሠጠን የተቀቀለ ሥጋ፣ ሩዝ፣ ከሽንኩርት የተሠራ ማባያ እናም አልጫ፣ ሁሉም ከተበላ በኋላ በሞካ ቡና ነው የምንጨርሰው:: ማታ ከመተኛታችን በፊት፣ ከኔ የእንግዳ ጠርሙሴ፣ መጠጥ አብረን እንጠጣለን:: እህ! ምን ትላለህ ፣ አልድ ቦይ?"

"ግሩም!" አልኩኝ፣ "የእሾንን ባርድ ቃላት በመዋስ፣ ከምግብ ፍላጎታችን ጋር ምግቡም በሰላም ይፈጭልን፣ ለሁለቱም ጤና ይስጠን!"

"ብራቮ! አው! አው! አ ማይ!" ብሎ ጮኸ:: መላጣውን እያሻሸ፣ ወደ ጎን የረዘመ ጢሙን እየጎተተ፣ ስሜት በተመላበትና በተነቃቃ ሁኔታ መሬቱን በእግሩ ይተመትማል::

መሀመድ፣ ሀሰን፣ ሃቢቡላህ እና አሊ ወዲያውኑ ሥራ ጀመሩ:: እሳቱም ነዶ ይወለበለብና ይንጣጣ ጀመር፤ ሠራተኞችም ወዲያና ወዲህ ይሯሯጣሉ፤



ቀኑ እያዘገመ በትህትና ወደ ምሽት ሲለወጥ፣ ላያችን ላይ የተጋተረው ገደልና ብዙኛው ሜዳ ለእይታችን እየተንሰራፉ በአረንጓዴ ቁጥቋጦዎች ተሸፍነው፣ እየጠለቀች ባለችው ፀሀይ ብርሃን መልበስ ጀመሩ፣ ይህም ለአይን ደስ የሚል ነገር ነበር፣ በዚህ ጊዜ ራት መድረሱ ተነገረ::

የቀረበው ምግብ ሁሉ በጣም ጣፋጭ ነበር:: ሁለታችንም ቢሆን ጥሩ የ ምግብ ፍላጎት ስለነበረን የበላነው ጤናማ ነው የሆነልን፤ ምግብ እየተበላም ማታውን ገፋ አደርግን አመሸን፤ ካፒቴኑም ስላጋጠመው አስደናቂ ገድሎቹ እያወራን ነበር፤ የፅጉር ያህል ከፍተት ሲቀር ከአደጋ ያመለጠባቸው ሁኔታዎች፣ የፍቅር ወሬዎች፣ በጨረቃ ብርሃን በህንድ ሜዳዎች ላይ ያደረጋቸው ግልቢያዎች፣ ከኒሎቲኮች ጋር ባጋጠመው ታሪኮች፣ ፋጢማና ዙሲካ በቀላሉ ታሪካቸው ሲገለጥ፤ የዶን ሁዋን ስሟ ካልታወቀ ሴት ጋር ያደረገው መተሻሸት፤ ተስፋ የሚያስቆርጡ ታሪኮች በሴባስቶፖል፤ ያም የካፒቴኑን የመሰለ ነጭ ፊት በኢንከርማን የምሽግ ጉድባ ለሁለት ሳምንት መጋደም፤ ከነዚህ የሁለት ሳምንታት ሞት የመሰለ ሰመመን ሰዎች እንዳዳኑትና፣ ከዚያም ደግሞ ለአንድ ወር በስኩታሪ ሆስፒታል አልጋ ላይ መከረም፤ የደፋሩ አረብ፣ ወደር የሌለው የነጂድ ጎሳዎች አሚር፤ ፈረሰኛ ሆኖ በተከሳሰ ምድር ከፌደራሎቹና ከኮማንቺዎች[72] ጋር ስላደረገው ውጊያ፤ ጤናማ ባልሆኑ ረግረጎችና ጫካዎች ስላደረገው ውጊያ፤ እና ሌሎችም አስደናቂና አስደሳች የሆኑ ታሪኮችን ጨምሮ ነው:: እነዚህ ሁሉ ታዲያ በፀሀፊ መልአክ ተመዝግበው በመፅሐፍ አልተፃፉም ወይ? ያለጥርጥር፣ ከሱ ሌላስ ማን የፎኖግራፊ አዋቂ አለ፤ እስዚያ እነዚህን አስገራሚ ታሪኮቹን ለመፃፍ በርግጥ አስተጋሪ መሆን አለበት፤ ይህም የዚህ የውድ ወዳጄ፣ ጀግናው የምግብ ጓዴ፣ የተከበረው የካፒቴን ስመልፈንገስ ታሪክ ነው::

ከአዲግራት ወደ ማይ ዋሂዝ ርቀቱ አስራ አራት ማይሎች ነበር:: በዚህ መንገዳችን ላይ ሰው መኖር በማይችልበት ቦታ ነው ያለፍነው:: ለሰባት ሰአታት መንገዳችን ላይ ያጋጠመን ፍርግሩግ ያለ የድንጋይ መንገድ በመሆኑ ለሰውም ሆነ ለእንስሳቱ አድካሚ ሆኖ ነው የተገኘው:: ነገር ግን፣ ማይ ዋሂዝ ለመድረስ ግማሽ መንገድ ላይ ስንደርስ እይታው ተቀየረ:: ሌላ ሜዳማ ቦታ፣ ልክ በአዲግራት እንዳየነው ተመሳሳይ ደረቅ ያለ ቦታ አይነት ፊት ለፊታችን ተዘርግቷል፤ ድርቀቱ ጠንከር ያለበት ቦታ ላይ አልፎ አልፎ በጥቂት አረንጓዴ ችግኞች ነፍስ ይዘራል:: በጋራው ጎንና ጎን የነበሩ የተከመሩ ድንጋዮችን ላለመነካካት ስንል ወደዚህ ቦታ ቁልቁል ስንወርድ በጥንቃቄ ነበር::

---

[72] በሰሜን አሜሪካ ከሚገኙ ተወላጆች (በተለምዶ ሬድ ኢንዲያንስ) ጎሳዎች አንዱ

ቁልቁለቱን ስንወርድ፣ ጠጠራማ የነበረው ስንጓዝበት የነበረው መንገድ ወዲያውኑ፣ በቀኝ በኩል፣ በተራራው ቀጥ ያሉ ገደሎች ወዳሉበት ወጣ ገባ ቦታ ይገባል፤ እነዚህ ወጣ ገባዎችም ብዛት ባላቸው ሥንጥቆች ተከፋፍለዋል፡፡ እነዚህ ሥንጥቆችና ቁጥቋጦዎች ደግሞ ጥሩ መደበቂያ ጫካዎች ይፈጥራሉ፤ በዚህ ቦታም ብዛት ያላቸው ሥጋ በል የዱር አውሬዎች ከተደበቁበት በሌሊት ምግብ ለመፈለግ ይወጣሉ፡፡

በጣም ደሀ የሆኑ ገበሬዎች፣ እንደ ጥንታዊ ሰዎች፣ እነዚህን ገደሎችና ዋሻዎች ከጨካኝና ፍርደ ገምድል ገዥዎቻቸው ለመደበቂያ የሚሆኑ ጥሩ ቦታዎች ሆነው አግኝተዋቸዋል፡፡ ነገር ግን፣ በነፃነት ሲኖሩ ድፍረትም ስለሚሰማቸው እናም በየጊዜው እየጠነከሩና ቁጥራቸው እየጨመረ ሲሄድ፣ ገበሬዎቹ ከራሳቸው መሀል አለቃ ይመርጣሉ፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ ራሳቸው የተጨቆኑ የነበሩት ወደ ጨቋኝነት ይቀየራሉ፡፡ በተሳኩ ዘረፋዎች ንብረት ካካበቱ በኋላ፣ ሊደረስባቸው በማይችሉ ከፍተኛ ቦታዎች የራሳቸውን መንደሮችና መከላከያዎች ይገነባሉ፤ አልፎ አልፎ ሲወጡም ያልጠረጠረ ገበሬን በማጥቃት፣ ንብረቱን፣ ሚስቱንና ልጆቹን ይወስዱበታል፡፡

በዚህ አካባቢ ላሉ ከተማዎች አሠራር ምክንያቱ ይህ ነበር፡፡ በዚህ አካባቢ ብቻ ሳይሆን በድፍን አቢሲኒያ የከተማዎች አመሠራረት በዚህ መልክ ነው፡፡ የአሁኑ አቢሲኒያ ሰዎች፣ ብዙ ምእት አመታት ወደኋላ ሳይኬድ፣ የብሪታንያ ጦረኛ ባሮኖችን ነው የሚመስሉት፡፡ ወይም፣ የደጋማው ሰዎች በሰላም በቆላው ቦታ የሚኖሩትን ሰዎች ተመላልሰው ሲያጠቁ፣ የራሂን የወንበዴ ባሮኖችና ካውንቶች ሲያደርጉት እንደነበረው ነው፡፡

ይህንን ሀሳብ ልሰጥ የቻልኩበት ምክንያት፣ ብዙ በመከላከያ የተሠሩ መንደሮች፣ እንደ አሞራዎች፣ ብዛት ባላቸው ሾጠጥ ባሉ ጋራዎች ላይ ከታች ደልደል ካለው ሜዳማ ቦታ በሁሉም አቅጣጫ ከፍ ብለው ተመሥርተው ስላየሁ ነው፡፡ አስፈላጊ ምግቦችን፣ እንደ እንቁላል፣ ቅቤ፣ ወተትና ዳቦ ለመግዛት ወደ እምባዎቹ ግርጌ ከተጠጋን፣ የእምባው ምልከት ነጋሪ ወይም የሚያስጠነቅቀው ሰው መናደዱን በማያሳስት ሁኔታ መግለፅ በሚቻል አነጋገር ሲጮህ እንሰማለን፡፡ በእያንዳንዱ አምባ ስር የውሃ ጉድጓድ አለ፤ በጉዟችን ላይ እነዚህ ብቻ ናቸው የመጠጥ ውሀ የሚገኝባቸው፡፡ እኛ ግን በአብዛኛው ለመጠጣ የማይሆን የተቋረ ውሃ እጠገብ ነበር ካምፓችን የምናደርገው፤ ይህም ምንም አማራጭ ስላለነበረን ነው፡፡ ጦሩ በቦታው አልፎ አስኪሄድና አቢሲኒያኞች ላይ የሚያስተማምን ነገር አስኪፈጥር ድረስ ለደህንነትም አስጊ ነው የነበረው፡፡

ጠዋት መንገድ ስንነሳ እናቆምበታለን ያልነውን ማይ ዋሂዝን ትተን፣ መንገዳችን ቀጠልንና በቂ ውሃ እንደልብ ወዳለበት ወደ አድ አባጋ ገፋን፡፡



አድ አባጋ የሚገኘው የሰሀን ቅርፅ በመስለ ጎድጓዳ ቦታ ሲሆን፣ ስፋቱ ሁለት ማይሎች ይሆናል፤ ዙሪያውን በተያያዙ ኮረብታዎች የተከበበ ሲሆን፣ በኮረብታዎቹ ላይ መንደሮች አሉባቸው፡፡ በመንደሮቹ የሚኖሩት ሰዎች አጥቂዎችና ጠብ ወዳዶች ናቸው፤ የሚገርመው ግን፣ በአብዛኛው አንዱ ካንዱ ጋር የተዛመደ ነው፡፡ እርስ በራሳቸው፣ በሚገርም ሁኔታ በሰላማዊ መንገድ አብረው መኖር ቢችሉም ከነሱ ውጭ ከሆነው ከቀሪው አለም ጋር ግን የሚሆን አይደለም፡፡

በዚህ ቦታ፣ ለአንድ ሌሊት ካምፕ አደረግንና፣ በነጋታው ከአድ አባጋ 12 ማይሎች ርቀት በሚገኘው ወደሚቀጥለው ጣቢያ ወደ ዶንጎሎ ገፋን፡፡ ይህ መንገድ የሚያልፈው ልዩ ስሜት በሚሰጥ ምድር ነው፡፡ ተከትሎ ለሚመጣው ሠራዊት ሲባል መንገዱ ብዙ ጉልበት ፈሰበታል፡፡ ለመጀሪያዎች ሶስት ማይሎች ብዙ ስሜት የማይሠጥ ፈዘዝ ባለ ያገሩ ከፍል ነበር የተጓዝነው፡፡ ዛፍና ቁልቁለት እየተፈራረቁበት፣ ሾጠጥ ያሉ የጎጆ ጣሪያዎች ያሉባቸው መንደሮች በየጋራው አናት ላይ ሆነው ይታያሉ፤ እነዚህ ደግሞ ከታች ከሚዳው ካሉ ሰዎች በኩራት የተለዩ መሆናቸው ነው፡፡

ከዛ ቀጥሎ፣ እጠር ካሉ የቁጥቋጦ ጫካዎች ተመንጥሮ በተሠራ መንገድ ላይ ተጓዝን፡፡ ከነዚህ ቁጥቋጦዎች በላይ የጥድና ሌላም ዛፎች ረዘም ብለው ይታያሉ፡፡ ቅርንጫፎቻቸው፣ እኩለ ቀን ላይ፣ ከምስራቅ ባህር ከደናኪል በረሀ አልፎ በሚመጣው ንፋስ ሲወዛወዙና ሲያጎነብሱ ይታያል፡፡ ከዚያ ቀጥሎ በየቦታው፣ አንዳንዶች ትልቅ፣ ሌሎችም አነስ ያሉ የድንጋይ ቁልሎች መገመት በማይቻልና በሚያደናብር ሁኔታ በየቦታው ተቀምጠው ይታያሉ፡፡ ወዲያውኑ ጨለም ባለ ሸለቆ አለፍን፤ በሸለቆው ጎንና ጎን ባሉ አናቶች ላይ፣ ጥቂት ሰዎች ብዛት ያለው ሠራዊት ማባረር የሚችሉባቸው ሥፍራዎች ናቸው፡፡ እንደገና በቁጥቋጦዎች በተሞላ ደን ውስጥ፣ ቀጥሎም ትልልቅ ዛፎች ያሉበት መንገድ ላይ ተጓዝን፤ በነዚህ ዛፎች ቅርንጫፎቻቸው ላይ ጦጣዎች የሚራወጡባቸው፣ ወፎች የሚዘምሩባቸው፣ ቀለማም የሆነው ወፍ ከንፉን በመዘርጋት ለአገሩ እንግዳ የሆኑ ነጭ ወራሪዎችን እንኳን ደህና መጣችሁ የሚል ይመስላል፡፡

የሚያሳዝነው ግን፣ ከነዚህ ዕይታዎች በተለየ፣ ግራጫ መልከና ጠቆር ያለ ገፅታ ያለው የአለት ቋጥኝ ፈጠጥ በማለት ይታያል፤ ፀጥ ያለም ሆኖ ላዩ ላይ ወፎችም አይዘሉበትም፣ ባለ ላባ ወፎችም አይዘምሩበትም ነበር፡፡

በነዚህ ዕይታዎች መሀከል በፍጥነት አለፍን፣ በመታጠፊያው ዙሪያ ግዙፍ የሆነው የባምባ ዛፍ ይታያል፤ ቅርንጫፎቹም በአቢሲኒያ ዝንጀሮዎች ተሞልቷል፤ ዝንጀሮዎችም በተጠጋን ቁጥር ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ለመግለፅ ያጉረመርሙ ነበር፤ ከዛም ወደ ሚቀጥለው ጋራ ጠቅለው በመውጣት ጥላቻቸውን በሚያስሙት ድምፅ ይገልፁ ነበር፡፡

የባምባ ዛፉንም አልፈን መንገዳችን በተራራ ዳገት ዙሪያ ወሰደን:: የተራራው አናት ከፍ ያለ በመሆኑ ደመናውን የሚጠቅስ ይመስላል፤ ቀና ብሎ ለሚያይ ሰው ራስ የሚያዞር ስሜት ይፈጥራል:: ዳገቱን አቀፍ አድርገን ዕይታችን ቀየርን፤ የተለያዩ ተራራውን የፈጠሩትን አለቶች ለማድነቅም ነበር:: በአግድሞሽ በደረጃ የተቀመጡትን የተራራውን ከፍሎችና የተለያዩ የድንጋይ አይነቶችን አይተን፣ ትንሽ ብርቅ የሆኑ ጠጠሮች ለቅመን የዶንጎሎ አረንጓዴ ሸለቆ አስኪታየን ድረስ መንገዳችን ቀጠልን:: በደንጎሎ በመሀሉ፣ ሁለት ወይም ሶስት ድንኳኖች ልክ የተከመረ ቾከ መስለው በሚመቸው ሳር ላይ ተተክለዋል::

አንድ ሌሊት በዶንጎሎ ካደርን በኋላ፣ የአስር ማይሎች ርቀት በመጓዝ ወደ አጉላ ወንዝ ሄድን:: ፀሀይዋ ገና በደንብ ሳትወጣ፣ ራሳችን በአንድ ኩባያ ሻይ ካረጋጋን በኋላ፣ አንደገና ዳገታማ፣ ወጣ ገባ የበዛበት ኮረብታ ላይ መንገድ ቀጠልን:: በሜዳዎች አቋርጠን፣ አረንጓዴ ሸለቆዎችን፣ በሸፍቶች መኖሪያና በገበሬዎቹ ዋሻዎች አድርገን ወደ ደቡብ አቅጣጫ ጉዞ ቀጠልን:: ፀሀይ ወጣችና የፈነጠቁት ጮራዎቿ ደግሞ ከፊት ለፊታችን የነበረውን መቀነት የመሰለውን ጭጋግ በመብሳት የሚያሸበርቅ ኅብረ ቀለም ያለው አሰደሳች ብርሃን ፈጥረውበታል::

የነበረው ጭጋግ ሲጠፋ፣ ጠቆር ያለ ጥላ ያላቸው በቁልቋል የተሸፈኑ የተራራ ሰንሰለቶች ከፍታቸው በሚለይ ሁኔታ ለኛ ተገለጡልን:: ከዚህ ቀደም ከአንድ ሰአት በፊት ያየነውን አድማስ አቋረጥን፤ ሆኖም ሌላ በደመና የታጠረ ኮረብታ፣ ጨለም ያለና አስፈሪ የሆነ ተተካብን:: ይህም፣ ባህር ብቻ ላየና የኢትዮጵያን ተራራዎች ላላየ ሰው የማይታመን ነገር ነው:: ከዚህ አልፎም ተሰፋፍቶና ተንጣሎ፣ በርቀት፣ ሌላ ምድርና ሰው ያልረገጠው በረሃ እንደሚኖር ተገንዝበናል:: ያም ሆኖ ፀሀይዋ ያለ ምህረት እናታችን ላይ ትወርዳለች፤ እንደገናም ተመሳሳይ ዕይታ ደግሞ ደጋግሞ ይታያል:: በትግስትና ምንም ሳያማርሩ፣ ከብቶቻችን የተረጋጋ ጉዞ ያደርጋሉ፤ ሙቀቱንም ሆነ ኩቻ ዋላዎች የሚያወርዱባቸውን ዱላዎች ቁብ የሠጡት አይመስልም::

ለመልፈንገስ ከትንሽ የመንገደኞች ቡድን ፊት ለፊት ቀደም ብሎ ነው የሚሄደው፤ ያደረገው ሰፋ ያለ ባርኔጣ ጭንቅላቱንና ፊቱን ሸፍኖታል፤ ምኑም አይታይም ነበር፤ ተኝቶ ይሆን እያለመመ ይሁን መገመት አልቻልኩም፤ ወይም ደግሞ አይኑን አፍጥጦ አካባቢውን እያስተዋለ፣ የነበረውን ፀጥታ አደፍርሶ፣ የሆነ ነገር ለማለጥ አይጠበቅ ይሆናል፤ የማያስደሰት ፀጥታ ነው፤ እኔም ከኋላ እየተከተልኩ ነበርኩ::

ፈረሴም ቢሆን፣ እኔ እንደተሰማኝና እንዳሳየሁት ሁኔታ በጣም የተከፋ ነው የመሰለው:: ሰማያዊውን ሰማይ አስተውዬ፣ እንደ ሁለት ጊዜም ቢሆን



ሀይለኛዋን ፀሀይ በአይኔ ጠቀስ አድርጌያለሁ፤ ከዚህም ጋር አድማሱን እየመላለስኩ ተመልክቻለሁ:: የበቅሎዎችን ማሰሪያዎች የጎደለ ነገር እንዳለ ብዬ በከንቱ ፈልጌ ነበር፤ የሠራኞችን ባህሪም በጥንቃቄ ተመለከትኩ፤ አሰቃው ማን መሆኑን ለማሳየት ለቅጣት የሚሆን ሰበብ እየፈለግሁ ነበር:: የካፒቴኑን ጀርባ እያየሁ በአእምሮዬ ብዙ ምስል እየፈጠርኩ ነበር፤ በሀሳቤም አሸንጌ ሀይቅ ላይ ከነትልቅ ባርኔጣው ቁጭ ብሎ ሲቀዝፍ አየሁት፤ እሱም ቢሆን ይህን አደርጋለሁ ብሎ ቃል ገብቶ ነበር::

ከሚያሰጨንቀው አሰልቺ ጉዞ እረፍ ለማለት ምን ማድረግ እችላለሁ? ጥያቄው በራሱ ተመለሰ:: በቀኑ በጠራራው ፀሀይ ሁለቱ አይኖቼ እንደተገለጡ፣ የቀን ህልም ጀመርኩ፤ በጣም የሚያምር፣ የምቾት፣ አዲስ ወይም እንግዳ የሆነ ነገር በመመኘት፣ የሚያነቃቃና የሚያስደስት ነገር እያሰምኩ ነበር::

ግራ የሆነ ሀሳብ በአእምሮዬ ብልጭ አለብኝና እኔም ሳቅሁኝ፤ በዚህ ጊዜ የእው አሊ በትልልቅ ጥቁር አይኖቹ ዞር ብሎ አየኝ፤ በመገረምም እየተመለከተኝ፣ "አሁን በሀበሻ ምድር ምን የሚያስቅ ነገር አገኘህ? ጌታው::" የሚል ይመስላል::

ካፒቴኑ ሾጠጥ ያለውን ጭንቅላቱን ሲያዞር፣ ጭንቅላቱ ላይ የነበረው ባርኔጣ እንደ ሙዚቃ ማጫወቻ ሸክላ አብሮ ዞረ:: በመደነቅ ሁኔታ ተመለከተኝ፤ እኔም ትንሽ እንደ ማፈር አልኩ፤ ነገር ግን፣ ከሱ አሻግሬ በርቀት ተመለከትኩኝ:: ከዛም፣ "ካምፕ! ካምፕ!" እያልኩ ጮህኩኝ:: የሚገርም ትንግሌ::

በቅሎዎችም እናፋ፤ ፈረሶችም አሰካኩ፤ ካፒቴኑም፣ ከሱ አፍ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁትን ዜማ፣ "ላ ላ ላ ቲ፣" በማለት መዘመር ጀመረ:: የአረቡ ሱሩጂና የህንዲስታኑ ኩቻ ዋላዎች በአራት ጥንድ ከንፈሮቻቸው የሚያላዝን አይነት ዜማ ማጉረምረም ጀመሩ፤ ነገር ግን ለትልቅ እፎይታና ከልብ የመነጨ ምስጋናም ለመግለፅ ነበር:: ይህም፣ ከካምፑ አጠገብ ወዳለው የወንዝ ዳርቻ ለንደርስ የተደገመ ነበር:: በአቢሲኒያ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየነው ይህ ወንዝ ከዋርካ ጥላ ስርና ከፈረሰ የቀድሞ ቤተመቅደስ አጠገብ ነበር::

ካምፓችን ያደረግንበት ይህ የፈረሰ ቤተ መቅደስ፣ በአስራ እንደኛው ክፍለ ዘመን አፄ ላሊበላ ቅዱስ ዶርካስ ለተባለ ለግሪክ ሰው ያሠራው ቤተ ክርስቲያን ነበር:: በዚህ ሀይማኖተኛ ንጉሥ በየቦታው ከተሠሩት ቤተ ክርስቲያናት አንዱ ነበር:: የመሀመዳን ኀላ የሆኑ ሰዎች እንደርታ ድረስ በመዝለቅ ባደረጉት ወረራ ምክንያት ቀስ እያለ እየፈራረሰ ነበር:: በዚህ አካባቢ የአጉላ ወንዝ ይወርዳል:: ለባጋዲስ ሥልጣን ሲይዝ፣ በዚህ ቦታ ብዙ

ንብረት ተቀብሯል የሚል ወሬ ስለሰማ ቦታው እንዲታሰስ ትዛዝ ሰጥቶ ነበረ:: በዚህ ንብርት ፍሲጋ ምክንያት ግንቡ መፍረስ ነበረበት::

ንብረቱም ተገኘ፤ ነገር ግን፣ ይህ ጥንታዊ ቦታ፣ ንብረት ፈላጊ ሠራተኞች ሲቆፍሩ አፈርሰው ትተውት በሄዱበት ሁኔታ ይገኛል:: ሁለት ምሰሶዎች ብቻ ነው ቆመው የቀሩት:: በአንዳንድ ክፍሉ፣ ከአምነበረድ የተሠራው ወለል እንዳለ ይታያል:: በዚህ በምንጓዝበት የሀገሪቱ ክፍል ወንዝ በጣም ስለማይገኝ፣ ወንዝ ተብዬውም ለአክብሮት ሲባል እንደ ስሙ ወንዝ ከተባለ፤ በጣም ፈጣን ትንሽ ወራጅ ውሃ ነበር:: ጥልቅ በተባለበት ቦታ የውሀው ከፍታ እስከ ቁርጭምጭሚት ብቻ ነበር፤ በጎን ግን ትንሽ ያርዶች ያክል ስፋት ስለነበረው እኛም ሆነ ከብቶቻችን ዘለን ገባንበትና ለአንድ ሰአት የሚሆንም ትንሽ ተንፈስ አልን::

በአጉላ ካምፕ፣ ኮሎኔል መርዌዘርንና የዘመቻው የተከበረ የጂኦግራፊ ባለሙያውን ሚስትር ክለመንት ማርክሀምን አገኘናቸው:: እንደሚታወሰው፣ ኮሎኔል መርዌዘር ወደ መቅደላ የሚወስድ ምቹ መንገድ ለማግኘት መጀመሪያ አቢሲኒያ ያረፈው የቃኝ መኮንን ነው:: ፊት ለፊት ከተገናኘን በኋላ፣ በኔ ዳኝነት፣ እንደሱ፣ ለተመደበበት ሥራ ትክክለኛ የሆነ ሰው ማግኘት ይከብዳል::

ፈጣን የሆነና አንቅስቃሴ የተላበሰው ይመስላል፤ በጣም የሚገርም ነገሮችን የማስተዋል ችሎታ አለው፤ ወሳኝና ፈጣን የሆነ መንፈስ ያሳያል:: የሲንዲ ሆርስ (ፈረሰኛ) የሚባለው የጦር ክፍል ኮሎኔል ነው፤ ነገር ግን ወደ አቢሲኒያ ከመምጣቱ በፊት በኤደን ተቀማጭ የፖለቲካ ሠራተኛ ነበረ:: ኤደን እያለ፣ ራሳም የሱ ፀሀፊ ነበረ፤ በሚስተር ሳያርድ ግፊት ነው እንግዲህ የአርመን ተወላጁ ራሳም ወደ ቴዎድሮስ መልክተኛ ሆኖ የተሾመው:: በኔ አስተያየት ያ ምርጫ ትክክል አልነበረም፤ ነገር ግን፣ መርዌዘር ሌላ የተሻለ አይገኝም በሚለው አምነቱ ፀንቶ ነበር::

ኮሎኔሉ ደግና ተወዳጅ ባህሪ የተላበሰ ነው፤ እንደዚህ ያለ ሰው ሲናገር፣ ምንም አይነት ስሜት የማየሳይ አና ስራም ሲያከናውን ምንም የተለየ ነገር የማያሳይ ሰው ማየት በጣም ደስ የሚያሰኝ ነበር::

እጉላ በቆየንባቸው በሶስቱ ቀናት፣ ካፒቴኑ ለአደን ወጣ:: እመሻሸ ላይ፣ የተለያዩ ያደናቸውን በደርዘን የሚቆጠሩ የአሞራ ዝርያዎች ይዞ ይመጣል:: ሶስት ክርክሮ ገድያለሁ ብሎ ተናግሯል፤ እኔ ግን እንድ እንኳን ማየት ብመኝም ያየሁት ምንም ነገር የለም:: በአራተኛው ቀን፣ ድንኳናችን ነቅለን፣ ጓዛችን ጠቅለን፣ ከብቶቻችን ጭነን ወደ እንጣሎ ጉዞ ጀመርን::



ከአጉላ ወንዝ ወደ አንጣሎ ያደረግነው ጉዞ ምንም የሚያስደስት አልነበረም:: በመጀመሪያው ቀን ማምሻውኑ ከእጉላ 19 ማይሎች ርቀት ቦታ የሚገኝ ዶሪሎ የሚባል ቦታ ደረስን፤ በሁለተኛው ቀን፣ 9 ማይሎች ርቀት ላይ እያኩለት ደረስን፤ በሶስተኛው ቀን ከ14 ማይሎች ጉዞ በኋላ አንጣሎ ገባን::



የግሪክ ቤተ መቅደስ ፍርስራሽ በአጉላ፣ የሰታንሊ ድንኳን

# ምዕራፍ አምስት

የናፒየር እዋጅ፣ ዲፕሎማሲ፣ ሜጀር ግራንት፣ የናፒየርና የመስፍኑ ካሳ ግንኙነት፣ የወዳጅነት ዕይታዎች

እኔና ሀይለኛው ካፒቴን በደስታና በተዝናና ስሜት ወደ አንጣሎ ስንጓዝ፣ ከጀርባችን ከትንሽ ርቀት በኋላ አንድ የእንግሊዝ ጄኔራልና የአቢሲኒያ መስፍን ዋና ተወናዮች የሆኑበት የሚገርም ትዕይንት እየተካሄደ ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ ለመግለፅ ከዚህ ምዕራፍ ውጭ በሌላ የመፅሐፉ ክፍል የተሻለ ቦታ አይገኝም፡፡

የተከበረው ሌፍተናንት ጄኔራል ሰር ሮበርት ናፒየር፣ የአቢሲኒያ ዘመቻ ጠቅላይ አዛዥ፣ አቢሲኒያ እንደገባ የሚከተለውን አዋጅ[73] ለገዥዎች፣ ለአለቆች፣ ለሀይማኖት መሪዎች እና ለአቢሲኒያ ህዝብ አስነገረ፡፡

*"ሁላችሁም እንደምታውቁት፣ የአቢሲኒያ ንጉሥ ቴዎድሮስ፣ የሦለጠኑ መንግሥታትን ህግ በመጣስ የእንግሊዝ አምባሳደር ካሜሩንን፣ የእንግሊዝ መልከተኛ ራሳምንና ሌሎችንም በእስር ይዟቸዋል፡፡ በወዳጅነት በተደረጉ ግፊቶች እስረኞችን ማስለቀቅ አልተቻለም፤ የሀገሬ መንግሥት እስረኞችን ለማስለቀቅ ጦር ይዤ እንደመጣ ትዛዝ ሰጥቶኛል፡፡ ለእስረኞች ወዳጅነት ያሳየ ወይም እነሱን ነፃ ለማውጣት የተባበረ ሁሉም ሰው ሽልማት ያገኛል፡፡ ነገር ግን እነሱን የሚጎዳ ማንም ሰው፣ የእንግሊዝ ጦር ወደ ሀገራችሁ በሚገባበት ጊዜ ከባድ ቅጣት ይደርስበታል፡፡ የአቢሲኒያ ህዝብ፣ ልብ በሉ፣ የእንግሊዝ ንግሥት በናንተ ላይ ምን ከፉ ሀሳብ የላትም፤ ሀገራችሁም ሆነ ነፃነታችሁ ላይ ምንም ዕቅድ የላትም፡፡ የሀይማኖት ቤቶቻችሁ፣ ሰዎቻችሁና ንብረታችሁ በጥንቃቄ እንዲጠበቅ ይደረጋል፡፡ ለወታደሮቼ የሚቀርብ ሁሉም ነገር ዋጋው ይከፈላል፡፡ ማንኛውም ሰላማዊ ኗሪ ጉዳት አይደርስበትም፡፡ ለእንግሊዝ ወታደሮች ወደ አቢሲኒያ መላክ ዋናው ተልዕኮ የግርማዊነቷን አገልጋዮች ነፃ ለማውጣትና ሌሎችም ያለአግባብ የታሰሩትን ለማስለቀቅ ነው፡፡ ይህ ተልዕኮ እንደተሳካ ጦሩ ወደመጣበት ይመለሳል፡፡"*

*"የአቢሲኒያን ግዛቶች በቋሚነት ለመያዝ ወይም በአገሪቱ መንግሥት ጣልቃ ለመግባት ምንም ፍላጎት የለም፡፡"[74]*

ፊርማ 'R. Napier.' (እር. ናፒየር)

[73] (በምዕራፍ አምስት ማስታወሻዎች)

[74] (በምዕራፍ አምስት ማስታወሻዎች)



ደጃዝማች ካሳ[75]፣ የትግሬው ራስ (በእንግሎ ሳክሶን አጠራር ጄኔራል ካሳ፣ የትግራይ ልዑል የሚል ማዕረግ በመስጠት) የዚህ በጥንቃቄ የተፃፈ ለሰለስ ያሰ አዋጅ ቅጂ ይደርሰዋል፡፡ ደብዳቤውን እንደተቀበለ ልዑሉ አድናቆቱን ይገልፃል፤ የደብዳቤውን ፀሐፊ፣ አለዚያም በእሱና በፀሐፊው መሀከል ግንኙነት ለመፍጠር ሥልጣን ያለው የፀሐፊውን መልከተኛ ማግኘት ይፈልጋል፡፡ የአዋጁ ፀሐፊ፣ በልዑሉ አገር አቋርጦ ወደመቅደላ ስለሚጓዝ፣ በሁለቱ መሀከል ወዳጅነት ቢፈጠር ትልቅ ፖለቲካ ጉዳይ ይሆናል፡፡ የሚቀጥለው ደብደቤ ከልዑል ካሳ ወደ ሰር ሮበርት ናፒየር የተላከ ነበር፤ እንደኔ ግምገማ፣ እንደ እንግሊዙ አዛዥ ደብዳቤ ሁሉ፣ የዚህም ቃላቶቹ በጥንቃቄ የተመረጡ ነበር...

*"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ፡፡*

*ደብዳቤ ተፃፈ ከደጃዝማች ካሳ፣ ርዕሰ መኳንንት ኢትዮጵያ፣ ይድረስ ለእንግሊዝ ወታደሮች አዛዥ፡፡ እንደምን አሉ? ደህና ነዎት ወይ?*

*በክርስቶስ ፈቃድ የአባቶቼን የሚካኤልን፣ የወልደ ስላሴን[76]፣ የሰባጋዲስን ዙፋን አስመልሻለሁ፡፡ ቀደም ብሎም ከቆንስል ሳልት ጀምሮ እስከ ቆንስል ፕላውደን ድረስ ወዳጆች ነበርን፡፡ ከእርስዎ ደብዳቤ አጠብቅ ነበረ፤ ሆኖም ስለዘገየ እኔ ራሴ ልኬያለሁ፡፡ የመጣችሁበትን ጉዳይ አላውቅም፤ ባውቅ ደስ ይለኛል፡፡ ወዳጆች ነን፡፡ የእኔንም የእርስዎን ቋንቋ በሚያውቅ ሰው፡ በአቶ ወርቄ ልጅ፣ በምርጫ[77] በኩል ለድጃለሁ፡፡ እኔ በልቤ ያለውን ልኬያለሁ፤ እርስዎም በልብዎ ያለውን ይላኩልኝ፡፡"*

*ተፃፈ 1860 አመተ ምህረት፣ ዘመነ ዮሐንስ፣ በህዳር 18፣ ረቡዕ ቀን፡፡*
*ፊርማ ደጃዝማች ካሳ[78]*
*ርዕሰ መኳኳንንት ዘኢትዮጵያ*

ከላይ በተጠቀሰው ደብዳቤ፣ እኛም እንዳመንበት፣ ልዑል ካሳ የልቡን ገልጧል፤ ሰር ሮበርት ናፒየርም በአብ፣ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም የልቡን እንዲገልጥ በትህትና ተጠይቋል፡፡

ስፖለቲካ ሲባልም ወደፊት እንደምንመለከተው፤ የእንግሊዙ ጄኔራል ተዋጊ ብቻ ሳይሆን አንደኛ ደረጃ ዲፕሎማት ስለሆነ፤ ሜጀር ጄምስ ግራንት፣

[75] (በምዕራፍ አምስት ማስታወሻዎች)

[76] ደጃዝማች ካሳ በአያታቸው በራስ ወልደ ሥላሴ በኩል ከጎንደር ነገስታት ይወለዳሉ

[77] (በምዕራፍ አምስት ማስታወሻዎች)

[78] (በምዕራፍ አምስት ማስታወሻዎች)

ሲ.ቢ፣ የናይል ወንዝ አሳሽና አዋቂ የሆነ ትልቅ ሰው ከብዙ አጅ መንሻ ጋር ወደ የኢትዮጵያው ርዕሰ መኳንንት ተላከ። ሜጀር ግራንት፣ እንደ እንግሊዙ አዛዥ ዋና መልከተኛነቱ መልካም አቀባበል ተደረገለት፤ በአከብሮት ተስተናግዶ በመጨረሻም በእንግሊዝና በትግራዩ አዛዦች መሀከል ግንኙነት እንዲደረግ ተወሰነ።

አቶ ምርጫ፣ የትግራይ አምባሳደር ሆኖ ወደ ናፒየር ተላከ። አምባሳደሩንም፣ ኮሰተር ያሉት ናፒየርና ረዳቶቹ ለዝግጅቱ ተገቢ በሆነ ሥነ ሥርአት በተመላበት ሁኔታ ነው የተቀበሉት። የተወሳሰቡ የወታደራዊ ሥርአቶች፣ የሻምላ ውድድር፣ ረዥም ምንጣፍ፣ ትራምፔት እየተነፋ፣ ታምቡርም እየተመታለት ነበር። ሥነ ሥርአት ያለው የትግሬው አምባሳደር ወደ አለቃው ተመለሰ፤ ነገር ግን ባየው ነገር በጣም ተገርሞና ተደንቆ፣ መቼም በሀሳቡ በርግጥኝነት እስከ ዛሬ ካያቸው ሰዎች እነዚህ ፈረንጆች በጣም የሚገርሙ ናቸው ማለቱ አይቀርም፤ ያ ደግሞ እውነታ አለው። ነገር ግን ይህን የወዳጅነት አዝማማሚያ ለሚጠራጠሩ ሰዎች፣ ካሳን እንደ ሮማዊው ፋቢየስ ከንከታቶር[79] አድርገው ነው ያዩት። መልከተኞች እንደገና ልከ ውጤቱን በርቀት ይከታተላል። መልከተኞቹ ያገኙትን ልባዊና መልካም አቀባበል ከንከታቶሩ ካሳ ከተመለከተ በኃላ፣ በመጨረሻ ሁለቱ "የቤት ወዳጆች" የሚገናኙበት ቀንና ቦታ ተወሰነ።

ሁለቱ ከሚገናኙበት ቀን ማምሻውን ቀደም ብሎ፣ ሰር ሮበርት ናፒየር የሁለተኛውን ብርጌድ ጦር በመያዝ አድ አባጋ የተባለውን ጣቢያ ይይዛል። የትግሬው አዛዥ ደግሞ ሀውዜን የተባለው ቦታ ካምፕ እንደሚያደርግ ነበር የተጠበቀው፤ ነገር ግን አላደረገም፤ ተዋጊው ሰር ሮበርት ናፒየርም የግድ አድ አባጋ ላይ መዘግየት ነበረበት። እራሱን "የኢትየጵያ ርእሰ መኳንንት" ብሎ የሚጠራው ያልሠለጠነ አለቃ እስኪመጣ ድረስ መጠበቅ ነበረበት። ለስምንት ቀናትም ጠበቀ፤ ተስፋ ቆርጦ ትዕግስቱ ባለቀበት ሰአት ሌላ መልከተኛ ደረሰና የሀውዜኑ ንጉሥ መምጣቱን አበሰረ።

በሚቀጥለው ቀን ሰር ሮበርት ናፒየር ከሚመቸው የአድ አባጋ ሸለቆ ካምፑ፣ 500 አግረኛ፣ 300 ፈረሰኛ፣ የተወሰኑ የሮያል ኢንጂኔርስ ሰዎች እና አራት 12-ፓውንደር የሚባሉ መድፎች አሰልፎ ወጣ። በጣም የተደራጀ አነስተኛ ጦር፣ ነገር ግን በማሾፍም አይነት የትግሬው መሰፍን ከጠበቀው የእንግሊዝ ጦር መጠን ያነሰ ወይም የተለየ ነበር።

79 (በምዕራፍ አምስት ማስታወሻዎች)





የደጃዝማች ካሳ መልከተኛና ተከታዮች
(Record of the Expedition to Abyssinia)

የሰናይደር[80] ጠመንጃዎችን ትከሻቸው ላይ አደርገው፣ ለአንድ ቀ የሚሆን ስንቅ በኮረጆታቸው ይዘው፣ የጦሩ ባንድ ከፊትለፊት ሙዚ እያሰማ፣ ይህ አነስተኛ ጦር መንገዱን ቀጠለ:: የሚያብረቀርቀው ጠመንጃቸው ከለበሱት ቀይ ዩኒፎርምና ካደረጉት የፀሀይ ባርኔጣ ጋር የሚንፀባረቅና አይ የሚያፈዝ ነው:: ብርጌዱ ጉዞ እንዲጀምር የትራምፔት ጥሪው ሲነፋ፣ ከብረ የተሠሩት አፎቶችና የፈረስ መኮልኮያዎች የመንኳኳት ድምፅ ያሰሙ ነበር::

ከነሱ ቀጥሎ ጥቂት መድፈኞች ተከተሉ፤ መጠናቸው አነሰ ያለ ለለነበ መድፎቹ ከበቅሎዎች ጀርባ ተጭነዋል:: ከኋላ፣ ኩምቢያቸውን ወደ ጎንና ጎ እያወናጨፉና እየተጎማለሉ ዝሆኖች ይከተላሉ፤ ከጀርባቸው ላይ ብዙ ሰዎ የሚይዘው ቤት የመሰለው ኮርቻና ከዝሆኖች ማጅራት ላይ የተቀመጡት የዝሆን መሪዎች(ነጂዎች) ይታያሉ::

የጦር አዛዡ ፈረሱ ላይ ተቀምጦ፣ ረዳቶቹ ደግሞ ባልሠለጠነው ሠራዊት አእምሮ ላይ አድናቆትን ለመፍጠር፣ ያላቸውን ጥሩ ልብሰ በመልበ ከሠልፈኛው ፊት ለፊት በሶምሶማ ይሄዳሉ::

በጥሩ ሥነ ሥርአትና ሲጀምሩ እንደበረው ቅልብጭ ያለ አሰላለፍ በደንብ የተደራጀው አነስተኛ ሠራዊት፣ ማይ ደብር ከተባለው የአፈሲል ግንኙነቱ የሚደረግበት ሜዳ ይደርሳል:: የሚያስደሰት ቦታ! በሁለቱ ሰዎ መሀከል ለሚደረገው የክብርና የመልካም ምኞት ልውውጥ በጣም አመቺ ቦ ነበር:: በዘርና በሃይማኖት ያን ያህል ይለያያሉ ወይ! በዚህ ግማሽ ማይል በማይሞላ ዙሪያ፣ አረንጓዴ የለበሱ ኮረብታዎችና ዳገቶች፣ መሐሉ ላይ ደግሞ ትንሽ ወራጅ ውሀ ያለበት የማይ ደብር ሸለቆ ነው::

ጠመንጃዎች መሬት ላይ ተደርድረው፣ ፈረሰኞቹ ከየፈረሶቻቸው ወርደው፣ ወታደሮችም ከሚወርደው ንፁህ ውሀ ከጠጡ በኋላ ሜዳው ላይ ተጋደሙ:: በሚገርም ሁኔታ ምንም የሀሳብ ምልከት ሳይታይባቸው የመስፍኑን መምጣት ይጠባበቃሉ::

ጄኔራሉና ረዳቶቹ በርጋታ ዳገቱን ወጥተው፣ የሚመጣውን አጀብ ለማየት ከፍ ካለው ቦታ ላይ ቆመዋል::

ራቅ ብሎ፣ ሜዳማ ቦታው፣ የቁልቋል ተክሎች አልፎ አልፎ እንደ ነጠብጣብ እየታዩበት የወይን ጠጅ ቀለም ባለው መልኩ ተንጣሎ ይታያል:: ተራራማው ደብር ደምባ በጫፎቹ ጠቆር ያሉ ደመናዎችን በሰቶ ይታያል፤ ከሜዳዎቹ፣ ከጎድጓዳ ስፍራዎችና አነስ ካሉ ኮረብታዎች በላይ የተለያዩ በድፍረት የቆሙ አምባዎች በተለያየ አቅጣጫ ይታያሉ::

[80] ሰናይደር ጠመንጃ





የእንግሊዞች ካምፕ በአድ አባጋ
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

ወደኋላ በኩል፣ አምባ ሹኩላት ፀጉሩን እንደተላጭ ግዙፍ ጃይንት በአናቱ የደመናዎችን ስብስብ በስቶ ይታያል፡፡ መስባ ተራራ ከፊት ለፊት ነበር፤ የአርንዲን ተራራ ደግሞ በጎንና በጎኑ የደንጎሎ ማለፊያን ይታከካል፣ ከፊት ለፊታችን ቀጥታ እንደ ጦር ቅርፅ ያለው ሌላ ከፍታ ስር ነጭ የኤተር ጋዝ የሚበንበት ይመስላል፡፡ አይደለም፤ ኤተር አልነበረም፤ አቧራ ነበር፡፡ የሚነፍስ ነፋስ አቧራውን ሲያስለቅቀውና የእንግሊዝ ቃፊር ፈረሰኞች ሲመለከቱ፣ ከማይ ድብር አጠገብ በሰማያት ላይ እንዳሉ ኮከቦች ከምችት ቀጥ የሚታየው የልዑል ካሳ ሠራዊት ነው፡፡

"ባለህበት! ሻንጣ በጀርባ፣ ጠመንጃችሁን ያዙ፣ ተሰለፍ! ወታደር በስነ ሥርአት! በሚቻል ሁኔታ በደንብ ሁኑ!" በቅፅበት፣ ትዛዙ ተፈፀመ፡፡ በደንብ የታጠቁ፣ ደመቅ ያለ ብርቱካንማ ልብስ የለበሱ እግረኛ ወታደሮች በመስመር ተሰለፉ፤ በቀኛቸው በኩል ፈረሰኛው፣ በግራ በኩል መድፎቹና ተኳሾች በተጠንቀቅ ቆሙ፡፡ ሰልፉም በሚያምር ሁኔታ በአንድ ትንሽ ወራጅ ውሀ አጠገብ ነበር፡፡

የእንግሊዞቹ አሣሾም በፍጥነት ወደድንኳኑ በመሄድ አለባበሱን አስተካከለ፡፡ ረዳቶቹ ድንኳኑን ዙሪያውን ከከበቡ በኋላ ምስጥራዊ ውይይት ተካሄደ፡፡ ከዚህ በኋላ ሶስት መኮንኖች፣ ሰማያዊና ብርማ ቀለም ያለው ዩኒፎርም በለበሰ በሶስተኛው ቀላል ፈረሰኞች ታጅበው ወደ መስፍኑ አቅጣጫ ሄደው የእንግሊዙ ጄኔራል ከሱ ጋር እኩል እንቅስቃሴ እንደሚጀመር ነገሩ፡፡

ታምቡሮችና አጠር ያሉ ለ ትዛዞች በተቃራኒ ባለው ከፍታ ቦታ ይሰሙ ጀመር፡፡ የአቢሲኒያውያን ጦር መንቀሳቀስ ሲጀምር፣ ሰልፉ ረዘም ያለ የፈረሰኛና የእግረኛ ጦር ይሆ ነው የቀረበው፡፡ ሁለት ወይም ሶስት የሚሆኑ እጃቸው ረዘም ያለ ጠንከር ያሉ ሰዎች ፊት ለፊት እየጋለቡ ይመራሉ፡፡ ደማቅ ቀለም ያለው ድንኳን ከተተከለ በኋላ አንድ ሰው ወደ ድንኳኑ ሲገባ ታየ፡ ምናልባትም መስፍኑ ይሆናል፡፡

ከአስር ደቂቃ ጉትትና ትግስት የተመላበት ጥበቃ በኋላ፣ መስፍኑ፣ ደመቅ ብሎ ያጌጠ ፈረስ ላይ ወጣ፤ አንድ የእንግሊዝ መኮንንም በፍጥነት እየጋለበ ለጄኔራሉ የመስፍኑን መምጣት ተናገረ፡፡

ጄኔራሉ ከድንኳኑ ሲወጣ፣ የአመት በአል ሪባኖች አልባሳት የተደረገበት ትልቅ ዝሆን በበሩ በኩል ቆሞ ነበር፡፡ ጄኔራሉም ዝሆኑ ላይ ተሣፈረ፡፡ በዚህ ዝሆንና ሌላም በሚከተል፣ በረዳቶቹም ተከቦና በፈረሰኞች ታጅቦ፣ ጄኔራል ናፒየር ወደ ወራጅ ውሃው አመራ፡፡





የደጃች ካሳና የሮበርት ናፒየር ግንኙነት
(ዋቢ. መጽሐፍ ተ.ቁ. 16)

መስፍኑ በቁልቁለቱ ሲወርድ፣ እንደ ክንፍ፣ በግራና በቀኝ በ500 የተመረጡ ተዋጊዎች ታጅቦ ነበር:: መልከኛ የሆነ ሰው የማዕረግ ጃንጥላ (ድባብ) በመስፍኑ ራስ ላይ ከትሮ ይዟል:: ጃንጥላው ወይንጠጅ ቀለም ያለው ሲሆን፣ በምርጥ ከፋይ የተሠራና ከብር በተሠሩ ጌጦች የተንቆጠቆጠ ነበር:: በቀኙ በኩል፣ ጋሻና ጦሩን የያዘ ረዳት አለ:: በግራ በኩል የትግራይ ታላቅ ሰው ልጅ የሆነ ጠመንጃ ያዥ አለ:: የጦር አለቆቹ፣ መስፍኑን ቀድመው በእግራቸው ይራመዳሉ፤ ከነሱ ፊት ለፊት መስፍኑን ለመገናኘት የሄዱት ሁለት የእንግሊዝ መኮንኖች ይመራሉ::

በዚች በትንሽ ወራጅ ውሃ ዳርቻ፣ ናፒየር ከተባባሪው መስፍን ጋር ተገናኙ:: ሁለቱም ከተሳፈሩበት ከወረዱ በኋላ፣ ወዳጅነት በሚያሳይ ሁኔታ ተቃቀፉ:: ይህም የአሜሪካ ኢንዲያኖች የሰላም ኮሚሽነሮችን እንደሚያቅፉት አይነት ነበር:: በዚህ አዲስ የጓደኝነት ትዕይንት፣ መስፍኑ ቁንጥንጥ ነበር፤ ናፒየር ግን ከሚገባው በላይ ረጋ በማለቱ ሞገስ ያለው ሁኔታም አላሳየም::

ሁለቱ፣ ማለትም ናፒየርና መስፍኑ ወደ ክብር እንግዳ መቀበያው ድንኳን ገቡ:: ካሳን ተከትለው የመጡ አምስት አለቆች፣ ጋሻ ያዡና ማዕረጋቸው የሚፈቅድላች ሰዎች ደርዘን ከሚቆጠሩ የናፒየር ረዳቶች ጋራ ወደ ድንኳኑ ገቡ:: በዚህ ጊዜም የክብር መድፍ ተተኮሰ፤ ይህ ሁኔታ ግን ከጋራው ማዶ ባሉ ሰዎችና ፈረሶች ግርግርና ድምፅ ፈጠረ:: በነዚህ ጠየም ያሉ ጦራቸውን ቀና አድርገው የያዙና ቀይ ዩኒፎርም የለበሱ የእንግሊዝ ወታደሮችን ቁልቁል የሚመለከቱ ሰዎች ላይ ያለመረጋጋት ምልክት ይታይ ነበር::

ከዚህ ቀደም የተጠቀሰው አምባሳደር አቶ ምርጫ፣ ሁሉም ከተቀመጡ በኋላ፣ በሁለቱ ባለሥልጣኖች፣ በእንግሊዙ ጄኔራልና በልዑል ካሳ መሀከል የሚገባው ፎርማሊቲ ልውውጥ እንዲጀመር በማድረግ የነበረውን ፀጥታ ቀየረው::

በግዛቱ በኩል፣ ወደ ደቡብ አልፈንበት የምንሄድበት የትግራዩ መስፍን፣ የለበሰው የሀር ቀሚስ ሆኖ እንደ የሴፍ ልብስ በአበባ ምስሎች የተዠጎረጎረ ነበር:: እናቱም ላይ ከአንበሳ ጋማ የተሰራ ጎፈር አድርጓል፤ ከጎፈሩም ሶስት ጉንጉኖች በጀርባው በኩል ወርደው ይታያሉ:: ጭንቅላቱ ደግሞ እግዚአብሔር ለአቢሲኒያኖች በርከት አድርጎ በሠጣቸው ፀጉር ተሸፍኗል:: ፀጉሩ ቅባት በደንብ የጠጣ ሲሆን እንደ ሹሩባ ተጎንጉኖ በአንገቱ ላይ ወርዷል:: በመስፍኑ አናት ላይ ደግሞ፤ ምንም ጠቆር ያለ ቢሆንም ከመጠን በላይ መልከኛ የሆነ ሰው ጃንጥላ ይዟል::

ካሳ ረጋ ያለና የወዳጅነት ገፅታ አለው፤ ሆኖም በሚያሳየው ቁርጠኛ ያልሆነ ባህሪ ምናልባትም "ያልተዘጋጀ ነው" ሊባል ይችላል::





*ደጃዝማች ካሳ ምርጫ*
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

ካሳ፣ "የፈረንጁን ንጉሥ በኔ ስም ሰላምታ አቅርብልኝ::" በማለት መልክተኛውን ምርጫን ጠየቀው፤ ምርጫም በጥያቄው መሠረት የጌታውን ቃል ትንሽ በማሳመር ለናፒየር ተናገረ::

ሰር ሮበርት ናፒየር፣ በተራው ሲመልስ፣ ካሳን በማየቱ ደስተኛ መሆኑን ገልፆ፣ የእንግሊዝ ክርስቲያን መንግሥት እንደራሱ የክርስትና ሀይማኖት እምነት የሚከተሉ ሰዎችን በአቢሲኒያ በማየቱ በጣም ደስተኛ መሆኑንም ገለፀ::

ካሳ ሲመልስም፣ በሀገሩ ፀጉረ ልውጥ ሰዎች ማየቱን እንደማይወድ፣ ነገር ግን እንግዳ መምጣት ካለበት ደግሞ ክርስቲያኖች ቢሆኑ እንደሚመርጥ ተናገረ::

ይህ አባባል በርግጥ በእንግሊዞች በኩል የወዳጅነት ስሜት እንዲፈጠር አላደረገም:: ምንም እንኳን በሜጀር ግራንት በኩል ዲፕሎማሲ ሥራ

በሲራም፣ የነዚህ ክሩሴደሮች[81] አላማ ላይ ብዙ ጥርጣሬ አለ፡፡ "ነገር ግን፣" አለ ሰር ሮበርት፣ "እዚህ ሀገር ብንመጣ፣ ምክንያቱ፣ መጥፎ ሰዎች ያገራችን ዜጎች እንደምርኮ በመያዛቸው ነው፡፡ ሰዎችን፣ ሁሉንም ካሰፈታን በኋላ ግዛታችሁን ሳንረብሽ ወደ ሀገራችን ተመልሰን እንሄዳለን፡፡"

"እሱስ ትክክል ነው፡፡" ብሎ ካሳ መለሰ፡፡ "ቴዎድሮስ ክፉ ሰው ነው፡፡ የሚገባውን ቅጣት እንደምትሠጡት ተስፋዬ ነው፡፡"[82]

ከዛም ጄኔራሉ፣ ካሳን ተከትለው የገቡትን ሰዎች ስም በትህትና ጠየቀ፤ አንደኛው ታላቅ ወንድም፣ ሁለቱ ደግሞ የካሳ አጎቶች መሆናቸውን አረጋገጠ፡፡ ሁሉም አለቆች ከወርቅ የተሠራ ሙሉ ክንዳቸውን የሚሸፍን አምባር የመሠለ ነገር አድርገው የአንበሳ ለምድ ደርበዋል፡፡

ለካሳ የመጡት ስጦታዎች ቀርበው መታየት ሲጀምሩ፣ መደበቅ የማይቻል አድናቆት በሁሉም ዘንድ ይታይ ነበር፡፡ ስጦታዎችም፣ በሎንደን ገርዷ የተሠራ አንድ ባለድርብ አፈሙዝ ነፍጥ፣ ከጠርሙስ የተሠሩ የቦሄሚያ ምንቸቶች፣ ከራሱ ሰር ሮበርት ጋጣ ደግሞ አንድ የአረብ ፈረስ ነበሩበት፡፡ ሁሉንም ስጦታዎች፣ ካሳ በተትረፈረፈ ምስጋና ተረከበ፡፡

ከዚህ በኋላ ስብሰባው ተዘጋ፤ ሁሉም አለቆችና የእንግሊዝ የጦር መኮንኖች ድንኳኑን ትተው ወጡ፡፡ ድንኳን ውስጥ የቀሩት ግን፣ ሰር ሮበርት ናፒየር፣ የጦሩ ፀሐፊና አንድ ረዳት ጄኔራል ባንድ በኩል፤ ልዑል ካሳና ቤተሰቦቹ፣ ከምርጫ ጋር በሌላ ወገን ነበሩ፡፡

ቀጥሎ የሆነውን በዝርዝር መግለፅ አይቻልም፡፡ ነገር ግን የዚህ ሚስጥራዊ ስበሰባ ውጤት የነበረው፣ የእንግሊዝ ወታደሮች በግዛቱ አልፈው እንዲሄዱ ካሳ ፈቃድ መስጠት፤ ከዛ በተጨማሪ ደግሞ በተቻለው አቅም በቀለብ እንደሚረዳ ነው፡፡ በርግጥ ቀለቡ በተመጣጣኝ ዋጋ በእንግሊዞ የጦር ኮሚሳሪያት የሚገዛ ነው፡፡ በመጨመር ደግሞ፣ ቴዎድሮስ ከተሸነፉ በኋላ፣ ለራሱ እርዳታ ስለሚያስፈልገው፣ ቢሰጠው ምኞቱ መሆኑን ገለፀ፡፡ ለዚህ፣ ሰር ሮበርት ቃል የገባው ሁሉንም ነገር ሲሆን፤ ነገር ግን፣ የመስፍኑ ተባባሪ ለመሆንና፣ መስፍኑን ሥልጣን ላይ የማውጣት ጉዳይ ላይ ግን የኢንግላንድን ንግሥት ትዛዝ የሚከተል መሆኑን፣ ማለትም ሰዎቹን ካስፈታ በኋላ ሀገሩን እንዳገኘው መልሶ እንደሚተውና የካሳን ምኞት ለሚሟላት ቃል እንደማይገባ ገለፀ፡፡

---

[81] ግብፃዊው የምፅዋው ገዥም ቢሆን፣ እንግሊዞቹ አገሪቱን የመውረር ሀሳብ አላቸው ብሎ መልክት ልኮ ስለነበር ለጥርጣሬው በቂ ምክንያቶች ነበሩት፡፡

[82] (በምዕራፍ አምስት ማስታወሻዎች)





ሌፍተናንት ጄኔራል ሮበርት ናፒየር
የአቢሲኒያው ጦር ጠቅላይ አዛዥ by John Watkins (1860s)

በዚህ ጉዳይ ላይ፣ ካሳም የግድ ሀሳቡን መቀበል ነበረበት፡፡ የእንግሊዞችን እርዳታ እሱ ማግኘት ካልቻለ፣ ሌላ ራስ ወይም ሥልጣን ፈላጊ ስለማያገኝ በዚሁ ረክቷል፡፡

መልካም ምኞትና የወዳጅነት መግባባት በሁለቱም ወገን አለቆች በኩል ከተፈጠረ በኋላ፤ ወይንና ሌሎች መጠጦችም ማሳለፍ ተጀምሮ ሁለቱም ወገኖች እርስ በርስ በመጨዋወት እንደ ሳክሶኖች "ዋስ ሄል[83]" የተባለ የባህል አጠጣጥ በኋላ ስብሰባው ተዘጋ፡፡

ወታደሮችም ለልዑሉና ለወታደሮቹ ታይታ ሰልፍ ማሳየት ጀመሩ፡፡ የብሪታንያ ወታደሮች በሰልፍ በመጓዝ ወደፊትና ወደኋላ ይመላለሳሉ፤ ወደ ግራም ወደቀኝም ይንቀሳቀሳሉ፤ ኮምፓኒ በረድፍ በታምቡርና በዋሽንት (ጥሩንባ)ና በሌላም ወታደራዊ ሙዚቃዎች በመመራት፣ ይህንን ትዕይንት አበክሮ የሚመለከተው እንግዳ በተመስጦ እሲያደንቅ ድረስ ትርኢት ያሳዩ ነበር፡፡

---

[83] 'Waes Hael'

ናፒየርም በተራው ከመሰፍኑ ጋር በመሆን ወንዙን ተሻግሮ የአቢሲኒያ ወታደሮችን ለማየት ሄደ፡፡

ወታደሮቹ ደህና ሰውነት ያላቸው ሆኖ፣ በደንብ የተዘጋጁና የአትሌቲክ እቋም ያላቸው ናቸው፤ በርግጥ መደበኛ ሳልሆን ጦርነት ሁነኛ የሆኑ ናቸው፡፡ ከአምስት መቶ እስከ ስድስት መቶ የሆኑት የተለያዩ ነፍጦች ይዘዋል፤ ጥንድ አፈሙዝ ያለው ነፍጥ፣ የሚለኮስ ነፍጥ[84]፣ የፖርቱጋል ፉሲሎችና የተለያዩ ሀገራት ነፍጦች ይዘዋል፡፡ ሌሎች እግረኞች ደግሞ እንደ እቅማቸው መጠን፡ ጦር፣ ጋሻና ጎራዴ ይዘዋል፡፡ በተራራማ ሀገር ወይም ቦታ፣ እነዚህ ሰዎች ከሌላ የሠለጠነ ወታደር ጋር አደገኛ ፍልሚያ ማድረግ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን፣ ይህ ሁሉ ጥሩ እሰላለፍ ቢኖራቸውም፣ ከአፄ ቴዎድሮስ ወታደሮች ፊት መቆም አይችሉም፤ አድርገውትም አያውቁም ነበር፡፡

ወታደሮቹን ካሰጎበኘ በኋላ፣ መስፍኑ፣ የእንግሊዙን ጄኔራል ወደ ሚያምረው ድንኳኑ እንዲገባ ጋበዘ፡፡ በድንኳኑም ውስጥ፣ ሁሉም ሰው መሬቱ ላይ በተነጠፈ ስጋጃ ላይ ተቀምጧል፡፡ ዳቦ፣ ጠጅ፣ እረቄና እህል ቀረበ፣ ሁሉም ተጋበዙ፡፡ ከመሄዱ በፊት፣ ካሳ፣ ጄኔራል ናፒየርን ታላቅ ጄኔራልና ታላቅ ሰው ነው በማለት ተናገረ፡፡ ከዚያም የራሱን ለምድ እውርዶ፣ የሜካውን ንጉሥ፣ የእንበሳውን ቆዳ የጄኔራሉ ትከሻ ላይ እለቀመጠ፡፡ የራሱን ጋሻና ጦርም ሰጦታ አቀረበለት፡፡ ጋሻው፣ በጎንደር ጥበበኛ የተሰራ ድንቅ ሥራ ነው፡፡ የጋሻው ወጣ ያለው መሀል ከፍሉ በወርቅ የተለበደ ነበር፤ የጋሻው ጠርዝ ደግሞ ቁጭ ቁጭ ባሉ ብዛት ባላቸው በወርቅና በብር በተሠሩ ጌጦች ተንቆጥቁጧል፡፡ ከመሀሉ ላይ የእንበሳ ጋማ ተንጠልጥሎበታል፡፡

ስለ እንግሊዝ ወታደሮች፣ የአቢሲኒያ ወታደር የሚያስበው፣ ግልጥ ሜዳ ላይ ከሆነ የእንግሊዝ ወታደሮችን ማጥቃት አይቻልም፤ ተራራማ ቦታ ላይ ከሆነ ግን ምንም ማድረግ አይችሉም ነው፡፡ በካምፓቸው ውስጥ ሲወራ እንደሰሙት ሳይሆን መድፎቹ እነስ ያሉ ናቸው፡፡ ከዚህ ሌላ ደግሞ የሰሙት፣ የእንግሊዝ ጦር፣ እያፏጨ የሚወረወር እሳት የሚተፋ መሳሪያ እንዳላቸውና፣ የሚወረወረው እሳት ደግሞ ሁለት ሶስት ማይል ርቀት ተወንጭፎ ቤት የሚያቃጥል መሆኑን ነው፡፡ እነዚህ መሳሪያዎች(ሮኬቶች) እንግሊዞች የሚተማመኑባቸው የመጨረሻ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ እንግሊዞች የዚህ አይነቱን መሳሪያ በብዙ ቦታዎች ተጠቅመውበታል፡፡ እንደ ንጉሡ ትልቅ መድፎች ባይኖራቸውም፣ በውጊያ ማሸነፍ ላይችሉ ሊቀሩ ወደነዚህ መሳሪያዎች ያዞራሉ፤ መሳሪያዎቹንም ማከሸፍ ወይም መከላከል ስለማይቻል

---

[84] Matchlocks ተጨማሪ ማስታዎች ምዕራፍን ይመልከቱ

ክብር መሠጠት የሚገባቸው ናቸው፡፡ ሰር ሮበርት ናፒየር እነዚህን የሚጠሉ የአርምስትሮንግ ሮኬቶች እውነተኛ ሀይል ለማሳየት ግማሽ ደርዘን የሚሆኑ አፋሮች ብቻ ተኮሰ፤ ከዚህም ዘላቂ ጠቀሜታ ሊገኝ ይችላል፡፡ ነገር ግን ስለ ቴዎድሮስ ሀይል፣ ወይም መቅደላ ላይ ምን አይነት ምሽግ እንዳላቸው በጣም ትንሽ ዕውቀት ነው ያለው፤ ስለዚህ የእነዚህ የጦር መሳሪያ ተተኳሾችን ሲሣይታ ሲል እስማባከኑን መርጧል፡፡

መሪዎቹ ከመለያየታቸው በፊት ተቃቀፉ፤ አንደኛው የሚችለውን ያህል ሌላውን ለመርዳት ቃል ገቡ፡፡